# መጽሐፈ ኢያሱ

ትምህርት ሁለት

## በድል አድራጊነት መውረስ

ተርጓሚ፡ እሸቴ በለጠ

THIRD MILLENNIUM MINISTRIES

Biblical Education. For the World. For Free.

© 2017 by Third Millennium Ministries
All rights reserved. No part of this publication may be reproduced in any form or by any means for profit, except in brief quotations for the purposes of review, comment, or scholarship, without written permission from the publisher, Third Millennium Ministries, Inc., 316 Live Oaks Blvd, Casselberry, Florida 32707.

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡ ሥርዓተ-ትምህርታችን በአሁኑ ወቅት ከ192 በላይ በሆኑ አገሮች ውስጥ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ጎብኙ፡፡

**ማውጫ**

1. መግቢያ

2. ለድል መዘጋጀት

   ሀ. አወቃቀርና ይዘት

   1. የእግዚአብሔር ትእዛዛት
   2. የኢያሱ ትእዛዛት
   3. የእስራኤላውያን መታዘዝ

   ለ. ቀደምት ትርጓሜ

   1. መለኮታዊ ሥልጣን
   2. የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን
   3. የሙሴ ህግ ልኬት (ስታንዳርድ)
   4. የእግዚአብሔር ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል
   5. እስራኤላውያን በጠቅላላ

3 . በሁለት ከተሞች ላይ የተገኘ ድል

   ሀ. አወቃቀርና ይዘት

   1. የኢያሪኮ ከተማ
      - የኢያሱ ሰላዮችና ረዓብ
      - የዮርዳኖስን ወንዝ በተዓምራት መሻገር
      - የኢሪኮ በተዓምር መፍረስ
   2. የጋይ ከተማ
      - የእስራኤላውያን መሸነፍ
      - የእስራኤላውያን ንስሓ መግባት
      - የእስራኤላውያን ድል ማድረግ
   3. የቃል ኪዳን ተሃድሶ

   ለ. ቀደምት ትርጓሜ

   1. መለኮታዊ ሥልጣን
   2. የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን
   3. የሙሴ ህግ ልኬት (ስታንዳርድ)
   4. የእግዚአብሔር ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል
   5. እስራኤላውያን በጠቅላላ

4. በሁለት መንግሥታት ላይ የተገኘ ድል

   ሀ. አወቃቀርና ይዘት

   1. የጣምራ ባላንጣ ኃይሎቹ ዳሰሳ
   2. የድሎቹ ዳሰሳ
   3. በደቡባዊ ባላንጣ ኃይሎች ላይ የተገኙ ድሎች
   4. በሰሜናዊ ባላንጣ ኃይሎች ላይ የተገኙ ድሎች

   ለ. ቀደምት ትርጓሜ

   1. መለኮታዊ ሥልጣን
   2. የሙሴ ህግ ልኬት (ስታንዳርድ)
   3. የእግዚአብሔር ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል
   4. እስራኤላውያን በጠቅላላ

5. ክርስቲያናዊ ተዛምዶ

   ሀ. አጀማመር

   ለ. እድገት

   ሐ. ፍጻሜ

6. ማጠቃለያ

# መግቢያ

በብሉይ ኪዳን ከሚገኙ መጻሕፍት መካከል የዘመናችንን ክርስቲያኖች ግራ ከሚያጋቡ ክፍሎች መካከል እስራኤል የተስፋቱን ምድር እንዴት እንደወረሰች መግለጫ የተሰጠባቸው በመጽሐፈ ኢያሱ ውስጥ የሚገኙ ምዕራፎች ከሁሉ በላይ ብዙዎችን ግራ የሚያጋቡ ናቸው፡፡ በክርስቶስ አማካይነት የምናውቀው አፍቃሪና ምህረትን የተሞላ አምላክ የከነዓንን ሰዎች ለማጥፋት የሚደርጉትን የእስራኤላውያንን ጥረት እንዴት ሊታገሰው ቻለ ብለን ግር ይለናል፡፡ የኢያሱ መጽሐፍ ግን ከእኛ ዘመነኛ አስተሳሰብ ተቃራኒ በሆነ መንገድ፣ ታገሳቸው ብቻ ሳይሆን፣ እስራኤላውያን ድል ያደርጉ ዘንድ አዘዛቸው፣ መራቸው እንዲያውም ኃይልን ሰጣቸው በማለት ጭራሹኑ እግዚአብሔር ከበረበት ይለናል፡፡ እኛም እንደ ክርስቶስ ተከታዮች፣ ልንቀበለው የሚገባን ይህንን አመለካከት ነው፡፡

በመጽሐፈ ኢያሱ ላይ ከምንመለከታቸው ተከታታይ ትምህርቶች መካከል ይህኛው ሁለተኛው ትምህርት ነው፡፡ “የእስራኤል በድል አድራጊነት መውረስ” የሚል ርዕስ ሰጥተነዋል፡፡ በዚህ ትምህርት የመጽሐፉን የመጀመሪያ ክፍል ማለትም ከምዕራፍ 1-12 ያለውን እንዳስሳለን፡፡

ቀደም ባለው ትምህርታችን፣ የመጽሐፈ ኢያሱን ቀደምት ትርጓሜ እንዲህ ብለን ጠቅለል አድርገን ተመልክተነው ነበር፡፡

> *መጽሐፈ ኢያሱ የተጻፈው በኢያሱ ዘመን ስለተከናወነው ስለ እስራኤላውያን በድል አድራጊነት መውረስ፣ ስለ ነገዶች የርስት ክፍፍል እና በቃል ኪዳን ስለመታመን በማንሳት ቀጣዩ ትውልድ በሚገጥመው ፈተና ከዚያ እንዲማር ለማድረግ ነው፡፡*

ቀድመን እንደተረዳነው፣ ኢያሱ በተቀዳሚነት የተጻፈው አንድም በመሳፍንት ዘመን፣ አሊያም በነገሥታት ዘመን ወይም ቢዘገይ በባሎን ምርኮ ወቅት ለኖሩ እስራኤላውያን ነው፡፡ መጽሐፉ ዒላማ ያደረገው በብሉይ ኪዳን ይኖሩ የነበሩት እስራኤላውያን በድል አድራጊነት ርስታቸውን ሲወርሱ፣ ለነገዶቻቸው የተሰጣቸውን ርስት  ለማጽናት ሲታገሉና ለቃል ኪዳናቸው ያላቸውን ታማኝነት ሲጸኑ በሚገጥማቸው ተግዳሮት አስፈላጊውን መመሪያ እንዲያገኙ ነው፡፡

የመጀመሪያው ዋና ክፍል ከምዕራፍ 1-12 ያለው፣ የሚተርከው ቀደምት ተደራሲያኑ ከውጊያ አንጻር ስለ ገጠማቸው ተግዳሮት ነው፡፡ ይህንን ሲያደርግ ትረካው ያተኮረው እስራኤላውያን ምድረ ከነዓንን ለመውረስ ወዳደረጉት የድል አድራጊነት ተከታታይ ግስጋሴ ትኩረታችንን በመሳብ ነው፡፡ እነዚህ ምዕራፎች በሦስት ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ፡ እስራኤል ለድል ያደረገችው ዝግጅት ምዕራፍ 1፤ ከምዕራፍ 2-8፣ እስራኤል በሁለት ከተሞች ላይ የተቀዳጀችው የመጀመሪያ ድል፤ ከምዕራፍ 9-12 ደግሞ ቆየት ብለው በሁለት ባላንጣ ኃይሎች ላይ ስለተቀዳጁት ድል የሚያወሱ ናቸው፡፡

በእስራኤል የድል አድራጊነት ውርስ ላይ ያተኮረው ትምህርታችን እነዚህን ሦስት ክፍሎች ይዳስሳል፡፡ መደምደሚያችንን ደግሞ በጥቂት የክርስቲያናዊ ተዛምዶ ሃሳቦች ላይ እናደርጋለን፡፡ አስቀድመን እስራኤል ለድል ስላደረገችው ዝግጅት እንመልከት፡፡

## ለድል አድራጊነት መዘጋጀት

እስራኤል ለድል አድራጊነት ካደረገቻቸው ዝግጅቶች መካከል ያለን ጊዜ የሚፈቅድልን ሁለቱን ብቻ ለመመልከት ነው፡፡ በመጀመሪያ የዚህን ክፍል አወቃቀርና ይዘት፣ ከዚያ ደግሞ የቀደምት ትርጓሜውን አንዳንድ ገጽታዎች እንቃኛለን፡፡ አስቀድመን አወቃቀሩንና ይዘቱን በወፍ በረር እንዳስስ፡፡

## አወቃቀርና ይዘት

መጽሐፈ ኢያሱ የሚጀምረው እስራኤልን በሞዓብ ምድር ላይ፣ በዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምስራቅ የሚገኝና በተለምዶ “ከዮርዳኖስ ማዶ” ተብሎ በሚጠራው ምድር ላይ ሰፍሮ እንደነበር በማሳየት ነው፡፡ እነዚህ ግዛቶች እጅግ ሰፊዎች ነበሩ፡፡ ዘኍልቍ 32 እንደሚነግረንም፣ የሮቤል፣ የጋድና የምናሴ ነገድ እኩሌታ፣ በዚያ ለመስፈር ለሙሴ ጥያቄ አቅርበው ተፈቅዶላቸው የሰፈሩባቸው ስፍራዎች ናቸው፡፡ በመጽሐፉ መግቢያ ላይ ግን፣ ኢያሱ ተነስቶ እስራኤላውያንን እየመራ ወደ

ምዕራብ በመጓዝ የከነዓንን ምድር ድል አድርጎ እንዲወርስ እግዚአብሔር ሲያዝዘው እናያለን፡፡ ያም ስፍራ በተለምዶ፣ “ከዮርዳኖስ ወዲህ” ተብሎ ይጠራል፡፡

እስራኤል ለድል አድራጊነት ዝግጅት ያደረገችበት ይህ ክፍል ወደፊት በተከታታይነት በሚመጡ ውጊያዎች ላይም የሚፈጸሙና ቅደም ተከተላቸው ተጠብቆ የሚከናወኑ የትዕዛዝ ሰንሰለቶችን የያዘ ነው፡፡

**የእግዚአብሔር ትእዛዛት**

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ለኢያሱ የሰጠውን ትዕዛዝ የምናነብበው በ 1፡1-9 ውስጥ ነው፡፡ በቁር 2፣ እግዚአብሔር ለኢያሱ “አሁንም አንተና ይህ ሕዝብ ሁሉ ተነሥታችሁ… ይህን ዮርዳኖስ ተሻገሩ፡፡” ከዚያም በቁጥር 6፣7፣ እና 9 ውስጥ፣ “በርታ ደግሞም ጽና” በማለት ኢያሱን ሦስት ጊዜ አዝዞታል፡፡

**የኢያሱ ትዕዛዛት**

በመቀጠል፣ ጸሐፊአችን ለእግዚአብሔር ትዕዛዛት ምላሽ በሚሆን መንገድ ኢያሱ የሰጣቸውን ትእዛዛት በ 1፡10-15 ውስጥ ያስተዋውቀናል፡፡ እስራኤላውያን ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ኢያሱ ያዝዛቸዋል፡፡ በቁጥር 11 ውስጥ፣ የህዝቡ አለቆች እስራኤላውያንን “ስንቃችሁን አዘጋጁ” በማለት እንዲያዝዙ ያደርጋል፡፡ በቁጥር 14 ውስጥ ደግሞ፣ ከዮርዳኖስ ማዶ የሰፈሩት ጽኑዓን ኃያላኑ ዮርዳኖስን ተሻግረው ወንድሞቻቸውን እንዲረዱ ያዝዛቸዋል፡፡

**የእስራኤል መታዘዝ**

በመጨረሻም፣ ጸሐፊአችን እስራኤላውያን ኢያሱን መታዘዛቸውን በ1፡16-18 ውስጥ ይዘግብልናል፡፡ በቁጥር 16 ውስጥ፣ ነገዶቹ ሁሉ በአንድ ድምጽ ታማኝነታቸውን ጠብቀው እንደሚያገለግሉና “ወደ ምትልከን ሁሉ እንሄዳለን” በማለት ለኢያሱ መልሰውለታል፡፡

እስራኤላውያን በድል አድራጊነት ለመውረስ ያደረገችውን ዝግጅት ባለሦስት ዘርፍ አወቃቀርና ይዘት ባለሦስት በልቡናችን አድርገን፣ አሁን ደግሞ በቀደምት ትርጓሜው ላይ አንድ ሃሳብ እንሰንዝር፡፡ ጸሐፊአችን መጽሐፉን በዚህ መንገድ ሊጀምረው ለምን ፈለገ?

# ቀደምት ትርጓሜ

መጽሐፈ ኢያሱ እስራኤል በድል አድራጊነት የከነዓንን ምድር ለመውረስ በምታደርገው ዝግጅት በጥሩ ቁመና ላይ ነበረች መሆኗን በማሳየት መጀመሩን ማስተዋል አዳጋች አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ቀጥተኛና አስተማማኝ ነበር፡፡ ሁሉም ነገዶች እንዲተባበሩ ኢያሱም ጥሪ አቅርቧል፡፡ ወደ ፍልሚያው ውስጥ ለመግባት ለቀረበው ጥሪ አዎንታዊ ምላሽ ለመስጠት ያመነታ አንድም እንኳን እስራኤላዊ አልነበረም፡፡ የኢያሱ ቀደምት ተደራሲያንም ባላንጣዎቻቸው ፊት ለፊት በሚጋፈጧቸው ወቅት ኢያሱና እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ትዕዛዛት እንዴት ምላሽ እንደሰጡ በማስተዋል እነርሱም ያንኑ መከተል እንደሚገባቸው በግልጽ ያስተውላሉ፡፡

**መለኮታዊ ሥልጣን**

ይህንን ምዕራፍ ይበልጥ ቀረብ ብለን ስንቃኘው፣ ጸሐፊአችን ያሰፈረው አዎንታዊ ቁመና በመጽሐፉ ውስጥ ተደጋግመው የተጠቀሱትን አምስት መሪ ሃሳቦች እንደሚያስተዋውቀን እንገነዘባለን፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ፣ በምዕራፍ 1 በዘገበው ለድል በተደረገው ዝግጅት ውስጥ፣ ከእስራኤል ዝግጅት በስተጀርባ ባለው መለኮታዊ ሥልጣን ላይ አፅንዖት ይሰጣል፡፡ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ትዕይንት የሚጀምረው በቁጥር 1 ላይ “እግዚአብሔርም ኢያሱን እንዲህ አለው” በሚሉት ቃላት ነው፡፡ ይህ ሐረግ ከኢያሱ ትዕዛዝ በስተጀርባ ያለው ሥልጣን እግዚአብሔር መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ከእነዚህ መስመሮች ጎን ለጎን፣ የሙሴ ተተኪ እንደሆነ ሰው እግዚአብሔር ራሱ በቁጥር 5 ላይ “ከሙሴ ጋር እንደሆንሁ፣ እንዲሁ ከአንተም ጋር እሆናለሁ” በማለት ሥልጣን ሰጥቶታል፡፡ ይህ መሪ ሃሳብ የእስራኤላውያን መታዘዝ በተመዘገበበት በቁጥር 17 ላይ እንዲህ

ተሰምሮበታል “በሁሉም ለሙሴ እንደ ታዘዝን እንዲሁ ለአንተ ደግሞ እንታዘዛለን፡፡” ቀደምት ተደራሲያኑ እስራኤላውያን ለድል ያደረጉትን ዝግጅት ልብ ሊሉ ይገባል ምክንያቱም እነዚህን ክንዋኔዎች ይመሩ የነበሩት እግዚአብሔርና የሙሴ ተከታይ እንዲሆን በመለኮት የተሾመው ኢያሱ ነበሩና ነው፡፡

**የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን**

በሁለተኛ ደረጃ፣ ኢያሱ ለድል ያደረገው ዝግጅት የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ የሚያስምር ነው፡፡ በእግዚአብሔር ትዕዛዛት የመጀመሪያ ትዕይንት ውስጥ፣ በቁጥር 6 ላይ እግዚአብሔር ኢያሱን እንዲህ ብሎታል፡ “ለአባቶቻቸው፦ እሰጣችኋለሁ ብዬ የማልሁላቸውን ምድር ለዚህ ሕዝብ ታወርሳለህና” ይህ ምንባብ እግዚአብሔር ለእስራኤል የገባውን ቃል ኪዳን በሁለት መንገዶች ያረጋግጣል፡፡ በመጀመሪያ፣ *nachal* (נָחַל) ከተሰኘው የዕብራይስጥ ቃል እንደምንረዳው፣ እስራኤል ከነዓንን ዝም ብላ መቀበል ሳይሆን “መውረስ አለባት”፡፡ የከንዓን ምድር የእስራኤላውያን ቋሚ “ርስት” እንደሆነች በዘዳግም መጽሐፍ ውስጥ ወደ ሠላሳ ለሚጠጉ ጊዜያት፣ በመጽሐፈ ኢያሱ ደግሞ ከአርባ ጊዜ በላይ ተጠቅሷል፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ በዚሁ ተመሳሳይ ጥቅስ ውስጥ ምድሪቱን እንደሚሰጣቸው “እሰጣችኋለሁ ብዬ ለአባቶቻቸው ምያለሁ” ተብሎ ተጠቅሷል፡፡ ይህም በዘፍጥረት 15 ውስጥ እግዚአብሔር ለአብርሃም ወይም በዚያን ወቅት “ለአብራም” ከነዓንን ለዘርህ እሰጣለሁ ብሎ የገባውን ቃል ኪዳን ያጣቅሳል፡፡ ከእስራኤል አባቶች ጋር እግዚአብሔር የገባው ቃል ኪዳን እንደሚያረጋግጠው፣ የከነዓን ምድር የተሰጠው በኢያሱ ዘመን ይኖሩ ለነበሩ እስራኤላውያን ብቻ ሳይሆን፣ መጽሐፉችን ለተጻፈላቸው ቀደምት ተደራሲያንም ጭምር ነው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ እግዚአብሔር ኢያሱን እንዳዘዘው ሁሉ፣ እነርሱም በዘመናቸው በብርታትና በወኔ ወደፊት ሊገሰግሱ ይገባቸው ነበር፡፡

**የሙሴ ህግ ስነ-ልክ**

በሦስተኛ ደረጃ፣ በየዘመናቱ የሚመጡ እስራኤላውያን ሁሉ በጦርነት ድል ማድረግና የተስፋዪቱን ምድር መውረስ ከፈለጉ የሙሴን ህግ ስነ-ልክ ማክበር እንዳለባቸው ጸሐፊው በግልጽ ያስቀምጠዋል፡፡ በቁጥር 7 መግቢያ ላይ፣ እግዚአብሔር ኢያሱን “ነገር ግን ጽና፥ እጅግ በርታ፤ ባሪያዬ ሙሴ ያዘዘህን ሕግ ሁሉ ጠብቅ፥ አድርገውም፤ በምትሄድበትም ሁሉ እንዲከናወንልህ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል።” ብሎ አዝዞት ነበር፡፡ የኢያሱ ድል አድርጎ የመውረስ ታሪክ ደጋግሞ እንደሚያነሳው፣ የመጽሐፉችን ቀደምት ተደራሲያን በሚገጥማቸው ፍልሚያ ውስጥ፣ የሙሴን ህግጋት መፈጸም ወደ ድል፤ አለመታዘዝ ግን ወደ ሽንፈት እንደሚያመራ የሚዘግበውን ወሳኝ አመለካከት ሙሉ በሙሉ ሊጨብጡት ያስፈልጋቸው ነበር፡፡

**የእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል**

በአራተኛ ደረጃ፣ ኢያሱ ለድል ያደረገው ዝግጅት የሚያመለክተን ከነዓንን በድል መውረሱ ተግባር በድል የተጠናቀቀው በእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል መሆኑን ነው፡፡ ይህንን አመለካከት የሚያጸናልን ሃሳብ የሚገኘው እግዚአብሔር ባስተላለፈው ትእዛዝ ውስጥ ሲሆን፣ እግዚአብሔር ኢያሱን እንዲህ ብሎት ነበር ቁጥር 5፡ “ከአንተ ጋር እሆናለሁ፡፡” ይኸው መሪ ሃሳብ በቁጥር 9 ውስጥ ተደግሟል በዚም እግዚአብሔር ለኢያሱ እንዲህ ብሎታል፡ “በምትሄድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው፡፡” 2ኛ ዜና 20፡17 የመሳሰሉ ምንባቦች እንደሚያመለክቱን፣ በውጊያ አውድማ ላይ እግዚአብሔር “ከህዝቡ ጋር ነው” ማለት በልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል አብሯቸው ነበር ወይም ስለ እነርሱ ይዋጋላቸው ነበር ማለት ነው፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ደግሞ፣ በኢያሱ 1፡17 እንደምናነብበው፣ የእስራኤላውያንን መታዘዝ እንመለከታለን፡፡ በዚያም የእስራኤል ነገዶች ሁሉ በአንድ ልብና በወኔ ለኢያሱ እንዲህ ብለውት ነበር፡ “አምላክህ እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር እንደ ነበረ ከአንተ ጋር ይሁን!” በውጤቱም፣ የእስራኤላውያን ድል ሰብዓዊ ጉዳይ ብቻ አልነበረም ማለት ነው፡፡ የእስራኤል የትኛውም ትውልድ በራሱ ብርታት ወደ ጦርነት የሚገባ አልነበረም፡፡ ድል የማድረግ ተስፋ የሚኖራቸው እግዚአብሔር አብሯቸው እና ስለ እነርሱ ከተዋጋ ብቻ ነበር፡፡

> በኢያሱ 1፡5 ውስጥ፣ እስራኤላውያን ምድሪቱን ለመውረስ ሲወጡ አብሯቸው እንደሚሆን እግዚአብሔር በኢያሱ አማካይነት ተስፋን ሰጥቷቸው ነበር፡፡ እናም፣ በእርግጥ፣ በምንም መንገድ ይሁን በየትኛውም

ዓይነት የእግዚአብሔር መገኘት እጅግ ትርጉም ያለው ጉዳይ መሆኑ ግልፅ ነው፤ የእግዚአብሔር አብሮነት መቼም ቢሆን እጅግ መልካም ነገር ነው፡፡ በዚያ ስፍራ ግን ከዚያ የዘለለ ነገር አለ፡፡ ምክንያቱም ቋንቋው የቅዱስ ጦርነት ሲሆን ተዋጊውም መለኮታዊ ነው፡፡ ዘጸአት 3 እና 6 በትክክል ከሚረዱት የብሉይ ኪዳን ምሁራን መካከል አንዱ እንደመሆኔ መጠን በዚያ ስፍራ ያህዌ ተብሎ ተብሎ የተጠቀሰው ቃል "የሠራዊት ጌታ" ለሚለው ሐረግ አጭር መግለጫ በው፡፡ ስለዚህ፣ ይህ ያህዌ የተሰኘው ስም፣ በብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሔር አገልግሎት ላይ ሚውለው ስም ሲሆን፣ ለህዝቡ የሚዋጋውን እግዚአብሔርን የሚገልጥ ስም ነው፡፡ እናም፣ "አማኑኤል" የተሰኘው ጭብጥ እኔ እንደሚመስለኝ፣ እግዚአብሔር በዚያ ስፍራ የተገኘው ሊያግዛቸው ወይም ሊያበረታታቸው ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በዚያ ስፍራ የተገኘው፣ የሰማይ ሠራዊቱን እየመራ ስለ እነርሱ ሊዋጋላቸው ነበር፡፡ ኢያሱና እስራኤላውያን በጠቅላላ ይጠበቅባቸው የነበረው የእግዚአብሔርን ምሪት መከተል ብቻ ነበር፡፡ ይህም የመጽሐፈ ኢያሱ ዋና መሪ ሃሳብ ነበር፡፡ ስለዚህ፣ በጥቅሉ፣ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር እንደሚሆን ብቻ ሳይሆን፣ ስለ እርሱ እንደሚዋጋላቸው የሚያስረግጥ ተስፋ ነው፡፡

- ሬቨረንድ፣ ሚካኤል ጄ፣ ግሎዶ

## እስራኤል ሁሉ

በአምስተኛ ደረጃ፣ የኢያሱ መግቢያ የሚያስተዋውቀን እስራኤል ሁሉ የመሳተፋቸውን አስፈላጊነት ነው፡፡ ቀደም ብለን እንደገለጥነው፣ ከዮርዳኖስ ማዶ ለሚኖሩ ነገዶች ሁሉ ኢያሱ ትዕዛዝ አስተላልፎ ነበር፣ ቁጥር 14 ላይ "ነገር ግን እናንተ፥ ጽኑዓን ኃያላን ሁሉ፥ ተሰልፋችሁ በወንድሞቻችሁ ፊት ተሻገሩ፥" ድል አድርጎ በመውረሱ ሂደት ውስጥ የእስራኤል ሁሉ ተሳትፎ በእስራኤል መታዘዝ በኩል እንደገና ተገልጦ ነበር፡፡ በቁጥር 18 "በትእዛዝህ የሚያምፅ ሁሉ… እርሱ ይገደል" በማለት እስራኤላውያን ለኢያሱ ምላሽ እንደሰጡ እናያለን፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ፣ ከዳር እስከዳር እንደምንመለከተው፣ ቀደምት ተደራሲያኑ በዘመናቸው በሚገጥማቸው ጦርነት ሙሉ በሙሉ ድል አድራጊ ለመሆን ከፈለጉ፣ እስራኤል በጠቅላላ እንደ አንድ ህዝብ ሊቆሙ እንደሚገባ ጸሐፊው ያሳስባቸዋል፡፡

እስራኤል ድል ለማድረግ ያደረገችውን ዝግጅት በግልጽ ማመልከት በኢያሱ ዘመን የተከናወነውን ድል በማድረግ የመውረስ ታሪክ ካስተዋወቀ በኋላ፣ እስራኤል በሁለቱ ከተሞች ማለትም በኢያሪኮና በጋይ ላይ የተቀዳጀቻቸውን ድሎች ወደ መዘገቡ ጸሐፊው ይሸጋገራል፡፡

# በሁለቱ ከተሞች ላይ የተገኙ ድሎች

በዚህ ደረጃ ላይ፣ መጽሐፋችን የሚያሳየን ኢያሱ ከነዓንን ድል ያደረገበትን የመጀመሪያ እርከን ነው፡፡ ኢያሱ ዐሥራሁለቱን የእስራኤል ነገዶች እየመራ የዮርዳኖስን ወንዝ በመሻገር ጌልጌላ ደርሰው ሰፈሩ፡፡ ከጌልጌላም በመነሳት፣ በኢያሱ መሪነት እስራኤላውያን ወደ ኢያሪኮ ገሰገሱ፡፡ ኢያሪኮንም ድል ካደረጉ በኋላ፣ ወደ ጋይ አቀኑ፡፡ ጋይን ድል ካደረጉ በኋላ፣ እስራኤላውያን የከነዓን እምብርት ወደሆነው፣ ወደ ገሪዛንና ወደ ኤባል ተራራ ገሰገሱ፣ በዚያም የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን በማደስ እነዚህን የጅማሬ ድሎች አከበሩ፡፡

እስራኤል በእነዚህ ሁለት ከተሞች ላይ የተቀዳጀቻቸውን ድሎች አስመልክቶ የተጻፈውን ዘገባ በሁለት ክፍሎች እንመለከተዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ አወቃቀሩንና ይዘቱን ከተመለከትን በኋላ ቀደምት ትርጉሙን ጠቅለል አድርገን እናያለን፡፡ በአወቃቀሩና በይዘቱ እንጀምር፡፡

### አወቃቀርና ይዘት

በጥቅሉ፣ በኢያሪኮና በጋይ ላይ የተደረገው ጦርነት በጣም እውቅ የሆነ የነገሮችን ተቃርኖ የምናስተውልበት ትምህርት ነው፡፡ ይህ ትምህርት ለጸሐፊአችን ትልቅ ፋይዳ አለው ምክንያቱም ሃሳቡ የመጽሐፉን ሩብ ያህል ይይዛልና ነው፡፡ ሁላችንም

እንደምናየው፣ ኢያሱ የሁለቱንም ከተሞች ጦርነት በድል የመራ ሲሆን፣ ወደ ድል ያቀናባቸው ጎዳናዎች ግን የተለያዩ ናቸው፡፡ በኢያሪኮ ላይ የተደረገው ጦርነት የትኛውም ገጽታ፣ ትርጉም የሚሰጥና አስደናቂ በሆነ መንገድ በእግዚአብሔር የተባረከ ነው፡፡ ነገር ግን በጋይ ላይ ተገኘው ድል የተሳካው ግን እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ከበደሉበት የከፋ በደል ንስሓ ከገቡ በኋላ ነው፡፡

## የኢያሪኮ ከተማ

እስራኤል በሁለቱ ከተሞች ላይ ተቀዳጀቻቸው ድሎች የተዘገቡት፣ በምዕራፍ 2-8 ሲሆን፣ በዋናነትም በሦስት ይከፈላሉ፡ የኢያሪኮ ከተማ በ2፡1-6፡27፣ የጋይ ከተማ በ7፡1-8፡29 እና የመዝጊያው የቃል ኪዳን ተሃድሶ በ 8፡30-35 ላይ ተመዝግበው ይገኛሉ፡፡ አስቀድመን እስራኤላውያን በኢያሪኮ ላይ የተቀዳጁትን ድል እንመልከት፡፡

የኢያሱ ሰላዮችና ረዓብ፡፡ የኢያሪኮ ታሪክ አራት ዋነኛ ክፍሎች አሉት፡፡ የሚጀምረውም በ2፡1-24 ላይ በተመዘገበው የኢያሱ ሰላዮችና የረዓብ ታሪክ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ላይ ኢያሱ ከተማይቱን የሚሰልሉ ሰላዮች ላከ፡፡ ወደ እስራኤል አምላክ ከተመለሰችው፣ ሰላቹን ከደበቀችውና አንዳችም ጉዳት እንዳያገኛት ቃል ኪዳን ከተገባላት ከረዓብ ጋር ተገናኙ፡፡ ሰላዮቹም እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ከተማይቱን አሳልፎ እንደሰጠ በልበ ሙሉነት በማመን ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ፡፡

ይህንን ጅማሬ ሚዛናዊ በማድረግ፣ አራተኛውና የመጨረሻው ክፍል የኢያሪኮን ታሪክ ይደመድመዋል፡፡ በ6፡22-27 ውስጥ ደግሞ፣ ትረካው እንደገና መለስ በማለት የኢያሱን ሰላዮችና ረዓብን ያነሳል፡፡ በዚህ ክፍል፣ ሰላዮቹ ለረዓብ ማለትም እርሷና ቤተሰቧ ተጠብቀው የእስራኤል ቤተሰብ እንዲሆኑ የገቡትን ቃል ኪዳን እንዲያከብሩ ኢያሱ ትዕዛዝ ያስተላልፋል፡፡ ጸሐፊአችን ረዓብንና ሰላዮቹን በመጀመሪና በመጨረሻው ላይ በማንሳት ከምዕራፍ 2-6 የተከናወኑት ጉዳች ሁሉ የኢያሪኮ ጦርነት አካል አድርጎ ያቀርበዋል፡፡

እንግዲህ፣ ዕብራውያን 11፡31 እና ያዕቆብ 2፡25 እንደሚያሳስቡን በመታዘዟ የተገለጠው፣ የረዓብ እምነት፣ ከእግዚአብሔር ቁጣ እንደታደጋት በማሰብ ልናመሰግን ይገባናል፡፡ ግን፣ ይህንን ምእራፍ በትልቁ አውድ ውስጥ ስናስቀምጠው፣ ጸሐፊአችን ለቀደሙት ተደራሲያን ፋይዳ የሚኖራቸውን ጉዳዮችም እንዳነሳ እናስተውላለን፡፡

ዮርዳኖስን በተዓምራት መሻገር፡ በእነዚህ የመጽሐፍ መደምደሚያዎች ውስጥ እጅግ ታላላቅ ተዓምራቶች የተመዘገቡባቸው ክስተቶችን እናገኛለን፡፡ በአንድ በኩል፣ እስራኤላውያን የዮርዳኖስን ወንዝ በተዓምራት መሻገራቸውን በ3፡1-5፡12 እናያለን፡፡ እነዚህ ምዕራፎች የሚጀምሩት እስራኤላውያን በምሥራቃዊው ዳርቻ ላይ ያደረጉትን የአምልኮተ እግዚአብሔር ዝግጅት ሲሆን፣ በተለይም ለእግዚአብሔር ባላቸው መሰጠትና እግዚአብሔርም አምልከውን በመቀበሉ ላይ ትኩረት በማድረግ ነው፡፡ ከዚያም ካህናቱ፣ የቃል ኪዳኑን ታቦት በመሸከም፣ ወደ ወንዙ ውስጥ ገቡ፣ የዮርዳኖስ ወንዝም ተከፈለ፡፡ አጋማሹ ላይ ሲደርሱም፣ ከካህናቱ በመቀጠል ዐሥራሁለት ሰዎች ሥራሁለት ድንጋዮችን አስቀመጡ፣ ህዝቡም በየተራ ተሻገሩ፡፡ ህዝቡ ሁሉ ከተሻገረ በኋላም ድንጋዮቹን ወደ ምዕራባዊው ዳርቻ ወሰዷቸው፣ ወንዙም ተመለሰ፣ ዐሥራሁለቱም ድንጋዮች በጌልጌላ ለመታሰቢያነት ተቀመጡ፡፡

በሥርዓታዊ ዝግጅቱ ላይ ካተኮረው ዘገባ በተመጣጠነ መንገድ፣ ኢያሱ በግርዘት እስራኤላውያን እንዴት አድርጎ እንደቀደሳቸው ጸሐፊአችን ዘግቦልናል፡፡ ከአራት ቀናት በኋላም፣ እስራኤላውያን የፋሲካን በዓል አከበሩ፣ ለመጀመሪያ ጊዜም በመና ምትክ የምድሪቱን ፍሬ በሉ፡፡

*የኢያሪኮ በተዓምራት መውደቅ፡፡* ይህ ርእስ ወደ ሦስተኛው ክፍል ማለትም በ5፡13-6፡21 ላይ ወደተዘገበው የኢያሪኮ በተዓምር መውደቅ እንሸጋገራለን፡፡ ጸሐፊአችንም ስለ ጦርነቱ ሲያስተዋውቀን የኢያሱ አስደናቂ ድል የተገኘበትን ምስጢራዊ ስልእላዊ መግለጫ ያቀርብልናል፡፡ ኢያሱ ወደ ኢያሪኮ ሲቃረብም፣ ከአንድ መልአክ ጋር ይገናኛል፣ በ5፡13 ላይም፣ ኢያሱ "ከእኛ ወገን ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ነህን?" በማለት ወሳኝ ጥያቄ አቀረበለት፡፡ በቁጥር 14ም፣ መልአኩ፣ "አይደለሁም፤ እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ አሁን መጥቼአለሁ" ሲል መለሰለት፡፡ ኢያሱም ራሱን

በትህትና ሲያቀርብ፣ የቆምከው በተቀደሰ ስፍራ ነውና ጫማህን ከእግርህ አውጣ በማለት መልአኩ ነገረው፡፡ በዚህም፣ ኢያሱ የሰማያዊ ሠራዊት ድጋፍ እንዳለው መልአኩ አረጋገጠለት፡፡

ከዚህ፣ ተዓምራዊ መገለጥ በኋላ፣ ኢያሪኮን የማጥቃቱ ሥራ እንዲጀመር እግዚአብሔር መመሪያ ሰጠ፡፡ ጥቃቱም ሙሉ በሙሉ የሚደገፈው በሰማያዊ ሠራዊት ነበር፡፡ እስራኤላውያንም የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙ ካህናትን በማስቀደም፣ ለስድስት ተከታታይ ቀናት የኢያሪኮን ከተማ አንድ ጊዜ ይዞሩ ነበር፡፡ በሰባተኛው ቀን ደግሞ፣ ከተማዪቱን ሰባት ጊዜ መዞረዋታል፡፡ ካህናቱ መለከቶቻቸውን በመንፋት፣ የመላእክቱን ሰራዊት ለውጊያ ይጣራሉ፡፡ ከዚያም ህዝቡ በታላቅ ጩኸት ወደ ከተማዪቱ የገቡት ኢያሪኮ ከወደቀች በኋላ ብቻ ነበር፡፡ እስራኤልም የእግዚአብሔርን መመሪያ ሙሉ በሙሉ አክብራለች፡፡

በኢያሱ ድል አድራጊነት ታሪክ ውስጥ ደግሞ ደጋግሞ የተጠቀሰውን የታሪኩን ይህኛውን ገፅታ መጥቀሱ እጅግ በጣም ወሳኝ ነው፡፡ በኢያሱ 6፡17፣ "ከተማይቱም በእርስዋም ያለው ሁሉ ለእግዚአብሔር እርም ይሆናሉ" በማለት ኢያሱ ትእዛዝ ያስተላልፋል፡፡ "ለእግዚአብሔር እርም" የሚለው ቃል ፍቺ *charam* (חָרַם) ከተሰኘው የዕብራይስጥ ቃል ጋር ይስማማል፡፡ ቀደም ባለው ትምህርታችን እንደጠቀስነው፣ ቃሉ በተጓዳኝ ከተቀመጠው ስም *cherem* (חֵרֶם) ጋር ተያይዞ የአምልኮን ተግባር የሚያመለክት ነው፡፡ ከጦርነት አውድ ውጪ፣ እንደ ዘሌዋውያን 27፡28 በመሳሰሉት ክፍሎች እንደተጠቀሰው፣ ተመሳሳይ የሆኑት የሰዎች፣ የእንስሳት፣ ወይም የመሬት መቀደስ ዓላማው ለአምልኮ አገልግሎት ነበር፡፡ በጦርነት አውድ ግን፣ በኢያሱ እንደምናገኘው ዓይነት፣ እንስሳትን ማረድና ሰዎችን፣ የተመረጡ ብረቶችን መለየት ለመገናኛው ድንኳን አገልግሎት ከመለየት ጋር ይያያዛሉ፡፡

እነዚህ ነገሮች ከአምልኮ ጋር የተያያዙ መሆኑን ለማመልከት፣ ቀደም ባሉት ጊዜያት ወታደሮች፣ የእስራኤልን ሠራዊት ጨምሮ፣ ከጦርነት በሚያገኙት ምርኮና ባሮች አማካይነት ራሳቸውን ባለጠጋ ያደርጉ ነበር፡፡ ነገር ግን ዘዳግም 20፡16 የመሳሰሉትን ምንባቦች ስንመለከት ግን፣ ከረዓብ በስተቀር፣ ጠቅላላውን የከነዓንን ዝርያ ለእርሱ እንዲቀድሱለትና በዚያም እንዲያመልኩት እግዚአብሔር ሲያዝዝ እናስተውላለን፡፡ እስራኤል ይህንን በማድረጓ፣ ድሉ በእርግጥ የእግዚአብሔር ድል እንደሆነ በእጅጉ እውቅና ሰጥታለች፡፡

## የጋይ ከተማ

ጸሐፊአችን የኢያሪኮን ድል ከዘገበልን በኋላ፣ በ7፡1-8፡29 ወዳሰፈረው እስራኤል በጋይ ከተማ ላይ ስላገኘችው ድል ይሸጋገራል፡፡

*የእስራኤል ሽንፈት፡፡* የጋይ ታሪክ በሦስት እርከኖች ይከፈላል፡፡ በመጀመሪያ፣ እስራኤል በጋይ ያጋጠማት ሽንፈት መግለጫ በ7፡1-5 ውስጥ፡፡ በዚህ ታሪክ፣ ጋይን በቀላሉ ድል ማድረግ ይቻላል በማለት ሰላዮቹ ለኢያሱ የተሳሳተ ምክር እንደሰጡት እናስተውላለን፡፡ ስለዚህ፣ እርሱም ለማጥቃት የላከው ጥቂት ወታደሮችን ብቻ ነበር፡፡ ደግሞም አካን የተባለው ሰው ለእግዚአብሔር ሊቀደስ የተገባውን ከኢያሪኮ የተገኘ ምርኮ በቤቱ እንደደበቀ እንገነዘባለን፡፡ በዚህም ምክንያት፣ የእግዚአብሔር ቁጣ ስለነነደደባቸው፣ በጋይ ውስጥ ሠላሳ ስድስት እስራኤላውያን ሞቱ የተቀሩት ደግሞ ተባረሩ፡፡

*የእስራኤል ንስሓ መግባት፡፡* በሁለተኛው እርከን፣ በ7፡6-26 ውስጥ፣ የእስራኤልን ንስሓ መግባት እንመለከታለን፡፡ ኢያሱ በእግዚአብሔር ፊት ያለቅሳል፣ እግዚአብሔርም የእስራኤልን የሽንፈት ምክንያት ይገልጥለታል፡፡ በ7፡11 እንደምናነብበው፣ የአካን በደል እጅግ የከፋ ስለነበር "እስራኤል፤ ... ቃል ኪዳኔን አፍርሰዋል" በማለት እግዚአብሔር ያውጃል፡፡ አካን የሚገኝበትንም መመሪያ እግዚአብሔር ያስተላልፋል፡፡ አካንም ኃጢአቱን ሲናዘዝ፣ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ መሠረት፣ እርሱ፣ ቤተሰቡና የእርሱ የሆነው ሁሉ "ለእግዚአብሔር መቀደሳቸውን" ለማመልከት ፈጽመው እንዲጠፉ ተደረገ፡፡ ከከነዓናውያን በከፉ በደላቸው ምክንያት እንዲመጣባቸው የታዘዘው ጥፋት በዚህ እስራኤላዊ ቤተሰብም ላይ ተፈጻሚ ሆነ፡፡

*የአካን ኃጢአት እጅግ አውዳሚ ኃጢአት ነበር፣ ምክንያቱም የእስራኤል ልጆች ኢሪኮን ድል ሲዲርጉ፣ ኢያሪኮን ድል በማድረጋቸው የሚገኘው ነገር ሁሉ ለጌታ የተቀደሰ እንዲሆን እግዚአብሔር ትእዛዝ አስተላልፎ ነበር... አካን ግን ለእርሱ ያልተገባውን ብቻ ሳይሆን፣ ለእግዚአብሔር የተቀደሰውንም ጭምር ነበርና ያደረገው ነገር እጅግ አሰቃቂ ነገር ነበር፡፡ እንግዲህ፣ ጉዳዩ አሰቃቂ የሆነበት ሌላው ምክንያት፣ እግዚአብሔር የሰጠው ቃል ኪዳን ከእስራኤል ጋር ብቻ የተያያዘ ነጠላ ቃል ኪዳን አልነበረምና ነው፡፡ መቼም እኛ በአስተሳሰባችን ግለኝነት ያጠቃናል፡፡ አንዳችን ለሌላችን ተጠያቂነት ያለብን እንደሆነ መገንዘብ ያስቸግረናል፡፡ አካን ሲበድል፣ የእርሱ በደል ብቻ ሆኖ አልተቆጠረም፣ በደሉ ህዝቡን በጠቅላላ ያነካካ ኃጢአት ሆነ ምክንያቱም እርሱ የዚያ አማኝ ማኅበረሰብ አካል ስለነበር ነው፡፡ ይህ ጉዳይ የብሉይ ኪዳን ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፣ የአዲስ ኪዳንም ጉዳይ ነው፡፡ ማለትም ሁላችንም አንዳችን ከሌላችን ጋር የተያያዝን ነን፣ እናም የአንዱ ሰው ጉዳይ ጠቅላላውን አካል ያውካል፡፡ እንግዲህ በእርግጥም በአካን በደልም የሆነው ይኸው ነው፡፡*

ዶ/ር ቲ.ጄ. ቤትስ

*የእስራኤል ድል፡፡* ሦስተኛው ክፍል፣ በ8፡1-29 የሚገኝ ሲሆን፣ የእስራኤልን የንስሓ ውጤት ያሳየናል፡፡ ያም እስራኤል በጋይ ላይ ያገኘችው ድል ነው፡፡ በዚያም የተለመደውን ንድፍ እንመለከታለን፡፡ ኢያሱ ሰዎች አድፍጠው እንዲቀመጡ እንዲያደርግ እግዚአብሔር ያዝዛል፡፡ ኢያሱም ህዝቡን ያዝዛል፡፡ ህዝቡም ይታዘዛል፡፡ ውጊያው ሲጀመርም፣ እግዚአብሔር በመለኮታዊ ጣልቃ ገብነት ለእስራኤል ድልን ሰጠ፡፡

## የቃል ኪዳን መታደስ

በኢያሪኮና በጋይ ላይ ድል ከተመዘገበ በኋላ፣ እስራኤል በሁለቱ ከተሞች ላይ የተቀዳጀቻቸው ድሎች የሚጠናቀቁት በ8፡30-35 በተመዘገበው የቃል ኪዳን ተሃድሶ ነበር፡፡ ሙሴ በዘዳግም 11፡29 ላይ የሰጠውን ትዕዛዝ በመፈጸም፣ እስራኤል የመጀመሪያውን የድል አድራጊነት እርከን ወደ ማክበሩ ተሸጋገረች፡፡ ያም የተስፋዪቱ ምድር እምብርት ወደሆኑት የኤባል ተራራና የገሪዛም ተራራ በመጓዝ የተደረገ ነው፡፡ የሙሴን ህግጋት በጠቅላላ አነበቡ፣ ጠቅላላ ህዝቡም የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን የመፈጸም ቃል ኪዳኑን እንደገና አደሰ፡፡

እስራኤል በሁለቱ ከተሞች ላይ የተቀዳጀቻቸውን ድሎች አወቃቀርና ይዘት በልቡናችን በመያዝ፣ አሁን ደግሞ የእነዚህን ምዕራፎች ቀደምት ትርጓሜ ወደ መመልከቱና ሃሳብ ወደ መሰንዘሩ እንሸጋገራለን፡፡

# ቀደምት ትርጓሜ

ምንም እንኳን ቀደምት ተደራሲያኑ በኢያሱ ዘመን ከገጠማቸው ችግሮች ለየት ያሉ ችግሮች እንደገጠማቸው የሚታወቅ ቢሆንም፣ ተደራያሲኑ ለእነርሱ ዘመን አገልግሎት ላይ ሊያውሏቸው የሚችሏቸውን ሃሳቦች ያገኙባቸው ዘንድ ጸሐፊው የኢያሪኮን ሃሳብ ያነሳል፡፡  የእግዚአብሔርን ህግጋት በመተላለፋቸው ምክንያት በጦርነት ድል ቢደረጉ ምን ሊያደርጉ እንደሚገባ ለማስተማር ሲል የጋይን ታሪክ ይዘግብላቸዋል፡፡ ቃል ኪዳናቸውን ለማደስ ያደረጉትን ክብረ በዓል ሲነሳላቸው በጦርነት ወቅት እግዚአብሔር ለህዝቡ በገለጸው ምህረት ተደራሲያኑ በመነካት በጦርነት ወቅት ድል ሲቀናቸው የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ለመጠበቅ ቃል ኪዳናቸውን እንዲያድሱ እያበረታታ ነው፡፡

### መለኮታዊ ሥልጣን

ጸሐፊአችን፣ በተደራሲያኑ ላይ በዚህ መንገድ ተፅዕኖ ለማሳደር ሲል፣ አንድ ጊዜ በድጋሚ እስራኤል በሁለቱ ከተሞች ላይ የተቀዳጀቻቸውን ድሎች በአምስት መሪ ሃሳቦች ላይ በማጠንጠን ይዘግብላቸዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃም፣ ከእነዚህ ድሎች ጀርባ ያለውን መለኮታዊ ሥልጣን አጽንዖት በመስጠት ይዘግብላቸዋል፡፡ የኢያሱን ወንዝ ሊሻገሩ ሲሉ፣ በ3፡7 ላይ “እግዚአብሔርም ኢያሱን.. አለው” የሚሉ ቃላትን እናነባለን፡፡ ልክ እንደበፊቱ ሁሉ፣ ሐረጉ የሚያጸናው ኢያሱ ህዝቡን አድርጉ ብሎ የሚያዝዘው  ትዕዛዝ ሁሉ  የእግዚአብሔር ሥልጣን ከበስተጀርባው እንዳለ ነው፡፡ በ6፡2 ላይ በተመዘገበው

ኢያሪኮ በተዓምራት በመውደቋ ታሪክም ውስጥ፣ "እግዚአብሔርም ኢያሱን አለው" የሚለው ሐረግ ተደግሞ እናገኘዋለን፡፡

ጸሐፊአችን መለኮታዊ ሥልጣንን አጽንዖት ሊሰጥበት ከመፈለጉ የተነሳ፣ ኢያሱ የሙሴ ተተኪ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የዮርዳኖስን ወንዝ በተዓምራት ሲሻገሩ፣ በ4፡14 እንደምናነብበው፣ እስራኤል ሁሉ "ኢያሱን በታላቅ ፍርሃት በማክበር ቆሙ" ያም ልክ ለሙሴ እንደነበራቸው አክብሮታዊ ፍርሃት ዓይነት ነው፡፡ በ4፡23 ውስጥ፣ "እስከንሻገር ድረስ አምላካችሁ የኤርትራን ባሕር ከፊታችን እንዳደረቀ እንዲሁ እስከትሻገሩ ድረስ አምላካችሁ እግዚአብሔር የዮርዳኖስን ውኃ ከፊታችሁ አደረቀ።" የሚል ተጽፎ እናነብባለን፡፡ ኢያሪኮ በተዓምራት ስትወድቅም፣ በኢያሱ 5፡15 ውስጥ፣ መልአኩ ኢያሱን "አንተ የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰ ነውና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ አለው"፡፡ ይህም በዘጸአት 3፡5 ውስጥ እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ዓይነት ነው፡፡

እንግዲህ የጋይን ከተማ ታሪክ ስንመለከት፣ እስራኤል ከመነሻው እግዚአብሔርን በታማኝነት ከማገልገል ጎድላለች፡፡ ነገር ግን እስራኤል ንስሓ ስትገባ፣ በ7፡10 እንደምናነብበው፣ "እግዚአብሔር ኢያሱን ... አለው"፡፡ "እግዚአብሔር ኢያሱን ... አለው" የሚለው ሐረግ እስራኤል በጋይ ላይ ድልን ስትቀዳጅም በ8፡1 እና 18 ላይም በድጋሚ ተጠቅሷል፡፡ ጸሐፊአችን እነዚህን ነገሮች አጽንዖት የሚያደርግባቸው፣ ተግባራቱ ሁሉ የተከናወኑት በእግዚአብሔር በራሱ መሪነት፣ ከዚያም የሙሴ ተተኪ በሆነው በኢያሱ ፈጻሚነት እንደሆነ ለተደራሲያኑ ለማሳየት ነው፡፡

## የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን

በሁለተኛ ደረጃ፣ እስራኤል በሁለቱ ከተሞች ላይ የተቀዳጀቻቸው ድሎች ታሪክ የሚያጸናው ከነዓን ለእስራኤላውያን መኖሪያ ሆና የተሰጠች የመሆኗን የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የሚያጸና ነው፡፡ የዮርዳኖስን ወንዝ ከተሻገሩ በኋላ በነበረው የስርዓት አከባበር፣ ከነዓን በ5፡6 ላይ "እግዚአብሔርም ወተትና ማር የምታፈስሰውን ምድር ለእኛ ይሰጠን ዘንድ ለአባቶቻቸው የማለላቸውን ምድር" ተብላ ተጠቅሳለች፡፡ ኢያሱ በላካቸው ሰላዮች ታሪክ ሲዘገብም ረዓብ በ2፡9 ላይ "እግዚአብሔር ምድሪቱን እንደ ሰጣችሁ" ብላለች፡፡ በ2፡24 ውስጥ ደግሞ ሰላዮቹ በልበ ሙሉነት ወደ ኢያሱ በመመለስ "በእውነት እግዚአብሔር አገሩን ሁሉ በእጃችን አሳልፎ ሰጥቶአል" በማለት ማረጋገጫ ሰጥተዋል፡፡ በተመሳሳይ መንገድም፣ በ6፡16 ውስጥ፣ የኢያሪኮ ግንብ ሲወድቅ፣ ኢያሱ የእስራኤልን ሠራዊት "እግዚአብሔር ከተማይቱን ሰጥቶአችኋልና ጮኹ" በማለት አዝዞ ነበር፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን አስመልክቶ የተዘረዘሩት የእነዚህ ዘገባዎች ዓላማ ቀደምት ተደራሲያኑ በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ቢሆኑ የተስፋዪቱን ምድር አስመልክቶ የተሰጣቸውን መለኮታዊ ስልጣን እንዲያረጋግጡ ማድረግ ነው፡፡

## የሙሴ ህግጋት ስነ-ልክ

በሦስተኛ ደረጃ፣ እስራኤል በሁለቱ ከተሞች ላይ የተቀዳጀቻቸው ድሎች ዘገባ ያሰመረው እስራኤል በጦርነት ድል ማድረግ የምትፈልግ ከሆነ የሙሴን ህግጋት ማክበር እጅግ ወሳኝ መሆኑን ማመልከት ነው፡፡ የዮርዳኖስን ወንዝ በመሻገራቸው ዘገባ ውስጥ፣ 4፡10 እንደሚነግረን "ሙሴም ኢያሱን እንዳዘዘው ሁሉ" ካህናት እስራኤልን መሩ ነበር፡፡ ኢያሱ 4፡12 ደግሞ "ሙሴም እንዳዘዛቸው" ነገዶቹ ሁሉ በየተራ እንደተሰለፉ እንገነዘባለን፡፡ በ5፡2 ደግሞ፣ እንደ ሙሴ ህግ ኢያሱ እስራኤላውያንን እንደ ገረዛቸው ይነግረናል፡፡ በ5፡10 ደግሞ፣ ሙሴ በደነገገው ቀን እስራኤላውያን ፋሲካን እንዳከበሩ እናነባለን፡፡ ተመሳሳይ በሆነ መንገድም፣ የኢያሱን ሰላዮችና የረዓብን ዘገባ ሲጠናቀቅ፣ በ6፡22 ውስጥ፣ ኢያሱ ሰላዮቹን "ሴቲቱንና ያላትን ሁሉ እንደ ማላችሁላት አውጡ" አላቸው፡፡ ያም በሙሴ ህግ የተደነገገ ስነ-ልክ ነው፡፡ በ6፡24 ደግሞ፣ "ከተማይቱንም በእርስዋም የነበረውን ሁሉ በእሳት አቃጠሉ" በማለት ሙሴ በዘዳግም ያዘዘው ነገር መፈጸሙን ጸሐፊው ይጠቁመናል፡፡

በተመሳሳይም፣ ለሙሴ ህግ ያለመታዘዝ ጉዳይ በጋይ በተከሰተው ሽንፈት ውስጥ ተብራርቷል፡፡ በ7፡1 "የእስራኤል ልጆች ግን እርም በሆነው ነገር በደሉ" በማለት በቀጥታ የሚሴን ህግ ማርከሳቸውን ያሳያል፡፡ በ7፡15 ደግሞ፣ አካን "የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን አፍርሶአልና" በማለት ኢያሱ እስራኤልን ወደ ንስሓ ጠርቷል የንስሓውንም ስርዓት መርቶታል፡፡ እግዚአብሔርም ደግሞ በ7፡13 ውስጥ የአካን እርም እስካልተወገደ ድረስ እስራኤላውያን በጠላቶቻቸው ፊት መቆም እንደማይችሉ ሲናገር ያለመታዘዙን ዳፋ አውጇል፡፡ ይህ ነጥብ እጅግ ወሳኝ ነው ስለዚህም ጸሐፊው በ22፡20 ላይ ተመልሶ ያነሳዋል፡፡ የእግዚአብሔር ቁጣ በእስራኤል ሁሉ ላይ የነደደበት ምክንያት "የዛራ ልጅ አካን እርም ነገር በመውሰድ ኃጢአትን ስለ ሠራ በእስራኤል ማኅበር ሁሉ ላይ ቍጣ አልወረደምን?" በማለት አብራርቷል፡፡ እርግጥ ነው፣ እስራኤል ፈጥና አካንን ስትለየው፣ ሽንፈቱ ወደ ድል ተለውጧል፡፡

ይህ አመለካከት እስራኤል ድል ካደረግ በኋላ በተካሄደው የቃል ኪዳን ተሃድሶ ወቅትም በድጋሚ አጽንዖት ተሰጥቶበታል፡፡ በ8፡31 ውስጥ፣ "የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ የእስራኤልን ልጆች እንዳዘዘ" እስራኤላውያን ተዘጋጁ፣ ደግሞም "በሙሴም ሕግ መጽሐፍ እንደ ተጻፈው፥ መሠዊያው ካልተወቀረና ብረት ካልነካው ድንጋይ" መሠዊያን ሰሩ፡፡

በ8፡32 ደግሞ፣ ኢያሱ የሙሴን ህግ በድንጋይ ላይ ጻፈው፡፡ እንደ 8፡33 ደግሞ፣ "የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ እንዳዘዘ" ህዝቡ በየተራ ቆሙ፡፡ በሙሴ ህግ ላይ ትኩረት የተሰጠበት ዘገባ በግልጽ የሚያመለክተው የእስራኤል ድልም ሆነ ሽንፈት የሚያያዘው ለሙሴ ህግጋት ከሚኖራቸው መታዘዝና አለመታዘዝ ጋር እንደሆነ ቀደምት ተደራሲያኑን ማሳወቅ ነው፡፡

> *ጠቅላላው የኢያሱ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን ህግ፣ ወይም የሙሴን ህግ ስለመታዘዝ እጅግ ጠንካራ ትምህርት የሚያስተምር መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፉ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ፣ መጽሐፉ በጠቅላላ ለመታዘዝ የቀረበ ጥሪ የያዘ ሲሆን፣ እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ምን ተከትሎ እንደሚመጣም ያሳያል፡፡ ገና በጅማሬው በ1፡8 ላይ፣ "የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፥ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው፤ የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ይከናወንልሃልም።" ተብሎ የተጻፈው በዚህ ምክንያት ነው፡፡"*

ፓስተር ዮርናን ክሩዝ፣ ተተርጉሞ የቀረበ

## የእግዚአብሔር ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል

በአራተኛ ደረጃ፣ እስራኤል በሁለቱ ከተሞች ላይ የተቀዳጀችው ድል በልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል ላይ አጽንዖት ያደርጋል፡፡ ይህ መሪ ሃሳብ እስከ ኢያሪኮ መፍረስ ድረስ በሚዘልቁ ምእራፎች ውስጥ ደግሞ ደጋግሞ ይታያል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል ስለ ኢያሱ ሰላዮችና ስለ ረዓብ የሚያወሳው ሲሆን፣ በ2፡9 ላይ ረዓብ "እናንተንም መፍራት በላያችን እንደ ወደቀ" በማለት እውቅና ሰጥታለች፡፡ በ2፡24 ደግሞ፣ ሰላዮቹ፣ "በአገሩም ውስጥ ያሉ ሰዎች ሁሉ በፊታችን ይቀልጣሉ አሉት፡፡" ዘዳግም 11፡22-25 የመሳሰሉ ምንባቦች እግዚአብሔር ደግሞ ደጋግሞ በእስራኤል ጠላቶች ላይ ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይሉን በመግለጥ በእስራኤል ጠላቶች ላይ ፍርሃትን እንደሚለቅቅባቸው ያመለክታሉ፡፡

ከዚህም ባሻገር፣ ዮርዳኖስን ሲሻገሩ፣ እግዚአብሔር ለኢያሱ እንዲህ ሲል አውጆለታል፡ 3፡7 "ከአንተ ጋር እሆናለሁ፡፡" ቀደም ብለን እንደጠቀስነው፣ ይህ መግለጫ የሚሳየው እግዚአብሔር በልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይሉ ለእስራኤል እንደሚዋጋ ነው፡፡ በ3፡10 ውስጥ፣ ኢያሱ የእግዚአብሔርን ቃል "ሕያው አምላክ በመካከላችሁ እንደ ሆነ" ወይም "ከእናንተ ጋር እንደሆነ" በማለት ለእስራኤላውያን አውጆላቸዋል፡፡ በ5፡1 ደግሞ፣ እግዚአብሔር የከነዓናውያን ልብ በፍርሃት እንዲቀልጥ በማድረግ ሲሠራ እናያለን፡፡

ከኢያሪኮ መውደቅ ጋር የተያያዙት እያንዳንዳቸው ክንዋኔዎች ደግሞ ይህንን መሪ ሃሳብ ይገልጣሉ፡፡ በተለይም በ6፡20 ውስጥ "ቅጥሩም ወደቀ" ተብሎ ሲጠቀስ በእግዚአብሔር ልእለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህም ጸሐፊአችን የኢያሱን ሰላዮችና የረዓብን ታሪክ ሲደመድም በ6፡27 ውስጥ "እግዚአብሔርም ከኢያሱ ጋር ነበረ" ማለቱ አያስደንቀንም ማለት ነው፡፡

ምናልባት እንደምንገምተው፣ እስራኤል በጋይ ውስጥ በገጠማት ሽንፈት ውስጥ የእግዚአብሔር ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል አልታየም፡፡ ይልቁኑ፣ በ7፡5 እንደምናነብበው "የሕዝቡም (የእስራኤላውያን) ልብ ቀለጠ" ይለናል፡፡ ሊቀልጥ የሚገባው ግን የከነዓናውያን ልብ ነበር፡፡ ግን በ7፡12 ውስጥ እግዚአብሔር እስራኤልን ወደ ንስሓ ሲጠራ፣ እግዚአብሔር ኢያሱን "ከዚህ በኋላ ከእናንተ ጋር አልሆንም" አለው፡፡ እስከመቼ? የአካንን እርም እስኪያርቁ ድረስ፡፡ እስራኤላውያን የአካንን እርም ካስወገዱ በኋላ ግን እግዚአብሔር እንደገና ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይሉን በጋይ ላይ በተገኘው ድል ገለጠ፡፡ በ8፡18 ውስጥ፣ እግዚአብሔር ኢያሱን፣ "ጋይን በእጅህ አሳልፌ እሰጥሃለሁና በእጅህ ያለውን ጦር በላይዋ ዘርጋ አለው" ከዚያም ጦርነቱ በድል ተጠናቀቀ፡፡

በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ፣ ጸሐፊአችን በሁለቱ ከተሞች ላይ ኢያሱ የተቀዳጃቸውን የመጀመሪያ ድሎች የተጠቀመባቸው ቀደምት ተደራሲያኑ ውጊያቸውን በሰብዓዊ ብርታት ማሸነፍ እንደማይችሉ ለማመልከት ነው፡፡ ድል ማድረግ የሚቻለው በእግዚአብሔር መለኮታዊ ኃይል ብቻ ነው፡፡

## እስራኤል በጠቅላላ

በአምስተኛ ደረጃ፣ እስራኤላውያን በሁለቱ ከተሞች ላይ የተቀዳጁቸው ድሎች ዘገባ፣ በድሉ መገኘት ውስጥ የሁሉም እስራኤላውያን ተሳትፎ እጅግ ወሳኝ መሆኑን አጽንዖት ይሰጠዋል፡፡ እስራኤላውያን የዮርዳኖስን ወንዝ ሲሻገሩ፣ 3፡1.17 እስራኤል በጠቅላላ ከኢሱ ጋር ተሻገሩ ይለናል፡፡ በ4፡14 ደግሞ፣ "እግዚአብሔር ኢያሱን በእስራኤላውያን ሁሉ ፊት ከፍ ከፍ አደረገው" ይለናል፡፡ በእርግጥም፣ በ4፡4 ውስጥ የተጠቀሱት "ዐሥራሁለቱ ሰዎች" እና በ4፡8፣9 እና 20 ውስጥ የተጠቀሱት "ዐሥራ ሁለቱ ድንጋዮች" የእስራኤልን ዐሥራሁለቱን ነገዶች ይወክላሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ በ5፡8 ውስጥ የእስራኤል "ህዝብ በጠቅላላ" በጌልጌላ ተገርዘዋል፡፡ ኢያሪኮ ሲደመሰስ፣ በ6፡3 ውስጥ እግዚአብሔር ኢያሱ "ሰልፈኞቹን ሁሉ" ይዞ በከተማዪቱ ላይ እንዲዘምት አዝዞታል፡፡

እንደገና ደግሞ፣ እስራኤል በጋይ ላይ በገጠማት ሽንፈት ተቃርኖውን ተመልክተናል፡፡ በ7፡3 ውስጥ፣ ሰላዮቹ ኢያሱን "ሕዝቡ ሁሉ አይውጣ" አሉት፡፡ የእስራኤላውያን ሁሉ ተሳትፎ በ7፡23 ውስጥ እስራኤል ንስሓ ገብቶ እስኪመለስ ድረስ አልታየም ነበር፡፡ በ7፡24 እና 25 ውስጥ ግን "እስራኤል በጠቅላላ" በአካን ላይ በተላለፈው ፍርድ ተሳታፊ ሆኗል፡፡

እዚህ ደረጃ ላይ ሁላችንም እንደምንጠብቀው፣ በቃል ኪዳን ተሃድሶው ወቅት፣ በ8፡33 ውስጥ፣ "እስራኤል በጠቅላላ" በእግዚአብሔር ፊት ቆሙ፡፡ ጸሐፊአችን በመጽሐፉ በዚህኛው ክፍል ውስጥ የእስራኤላውያንን በጠቅላላ በአንድነት መሳተፍ የጠቀሰው የሚመጣው የእስራኤል ትውልድ ሁሉ በአንድነት ለውጊያ ዝግጁ ሆኖ የመሰለፉን ወሳኝነት ያለ አንዳች ጥርጣሬ ግልጽ ለማድረግ ነው፡፡

የእስራኤል በድል የመውረሷ ነገር ለድል በሚደረግ ዝግጅት እንዴት እንደጀመረና ሁለቱን ከተሞች ድል ወደማድረግ እንዴት እንደተሸጋገረ ከተመለከትን አሁን ደግሞ፣ እስራኤል በሁለቱ ጣምራ ጠላቶቿ ላይ እንዴት ድልን እንደተቀዳጀች ወደሚተርከው ክፍል እንሸጋገራለን፡፡

# በሁለቱ ጣምራ ጠላቶች ላይ የተገኙ ድሎች

የኢያሱ መጽሐፍ ጸሐፊ ኢያሱ የተስፋዪቱን ምድር ድል አድርጎ የወረሰበትን የተቀረውን ታሪክ በተለያዩ በርካታ መንገዶች ሊያዋቅረው ይችል ነበር፡፡ ምርጫ ያደረገው ግን የኢያሱ ድል አድራጊነት ከሁለት ከተሞች ወደ ሁለት ክልሎች፣ ማለትም ወደ ተስፋዪቱ ምድር ደቡባዊና ሰሜናዊ ክልሎች እንዴት እንደተሸጋገረ መዘገቡን ነው፡፡ ወደፊት እንደምናየው፣ የመጽሐፉ ይኸኛው ክፍል በተለይ ለቀደምት ተደራሲያኑ እጅግ ወሳኝ ክፍል ነው፣ ምክንያቱም የኢያሱ ድል አድራጊነት እግዚአብሔር ለእስራኤል ተስፋ የገባላትን ድንበር ሙሉ በሙሉ እስኪያስከብር ድረስ የዘለቀ መሆኑን ስለሚያሳይ ነው፡፡

በመጽሐፋችን ውስጥ ከምንገኝበት ከዚህኛው ነጥብ ቀደም ብሎ፣ የእስራኤል ድል አድራጊነት የዘለቀው፣ ከዮርዳኖስ ማዶ እስከ ኢያሪኮ፣ ከዚያም እስከ ጋይ፣ ከዚያም እስከ ኤባልና እስከ ገሪዛም ተራራ ድረስ ነበር፡፡ በዚህ ክፍል ግን፣ ጸሐፊችን የሚያነሳልን ሃሳብ እንደሚሳየን በከንዓን ዙሪያ ያሉ መንግሥታት መጀመሪ በደቡብ ከዚያም በስተሰሜን ያሉት በኢያሱ ላይ በአንድነት ለመዝመት እንደተባበሩበት ነው፡፡

እስራኤል በእነዚህ ሁለት ጣምራ ጠላቶች ላይ የተቀዳጀቻቸውን ድሎች ስንዳስስ፣ የክፍሉን አወቃቀርና ይዘት ደግሞም ቀደምት ትርጓሜውን በስሱ ዳስ እንዳርጋለን፡፡ እስኪ አስቀድመን አወቃቀሩንና ይዘቱን በወፍ በረር እንመልከተው፡፡

# አወቃቀርና ይዘት

በምዕራፍ 9-12፣ የሚገኘውና እስራኤል በሁለቱ ጣምራ ጠላቶች ላይ የተቀዳጀችው ድል ዘገባ፣ በመጠኑ ግራ ያጋባል ምክንያቱም ምዕራፎቹ በርካታ የተለያዩ ጉዳዮችን ስላካተተ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ክፍል በአራት ዋና ክፍሎች እንደተዋቀረ ማስተዋላችን በጣም ይጠቅመናል፡፡

## የጣምራ ጣላቶቹ ወፍ በረር ዳሰሳ

በመጀመሪው ክፍል፣ 9፡1 እና 2፣ የእስራኤል ተቀናቃኝ ሆነው ስለቆሙት ሁለቱ ጣምራ ጠላቶች አጭር መግለጫ እናገኛለን፡፡ ይህም በሚቀጥሉት ምዕራፎች ምን እንደሚከናወን በአጭሩ ያስተዋውቀናል፡፡ እነዚህ ጥቅሶች፣ “በዮርዳኖስ ማዶ በተራራማው በቈላውም በታላቁ ባሕር ዳር በሊባኖስም ፊት ለፊት የነበሩ ነገሥታት ሁሉ … ኢያሱንና እስራኤልን ሊወጉ አንድ ሆነው ተሰበሰቡ።” ይሉናል፡፡

## የድሎቹ ዳሰሳ

የጣምራ ጠላቶቹ አራተኛና የመጨረሻ ክፍል የሆነው፣ በ 11፡6-12፡24 የሚገኘው ክፍል፣ የእስራኤልን ድሎች በአጭሩ በመዳሰስ በመግቢያው ላይ የተነሳውን ሃሳብ አመዛዝኖ ያቀርብልናል፡፡ ለመጀመር ያህልም፣ በ11፡16፣ 23 ከዮርዳኖስ መለስ በደቡባቢውና በሰሜናዊው ግዛቶች የተገኙትን ሰፊ ድሎች እንድናይ ያደርጉናል፡፡ ይህ ዘገባ ኢያሱ እግዚአብሔር አጥፋ ያለውን ሁሉ እንዳጠፋ አጽንዖት ሰጥቶ ሳየናል፡፡ በቁጥር 23 ላይም “ምድሪቱም ከሰልፍ ዐረፈች።” በሚለው ሃረግ ክፍሉ ይደመደማል፡፡ ይህንን ተከትሎም፣ በ12፡1-24 ውስጥ፣ የመጽሐፋችን ጸሐፊ ከዮርዳስ ማዶና ከዮርዳኖስ መለስ፣ እስራኤል ድል አድርጋ የያዘቻቸውን መንግስታትና ምድሮች ዝርዝር በማስፈር ይህንኛውን የመጽሐፉን ክፍል ይደመድመዋል፡፡

## በደቡባዊ ጣምራ ጠላቶች ላይ የተገኙ ድሎች

በእነዚህ ሁለት የመጽሐፍ መደምደሚያዎች ውስጥ፣ ሁለት ዋና ክፍሎችን እናገኛለን፡፡ የመጀመሪያውም በ9፡3-10፡43 የሚገኘውና ጸሐፊአችን እስራኤል በደቡባዊ ጣምራ ጠላቶች ላይ የተቀዳጀችውን ድል የሚዘግበው ነው፡፡ እነዚህ ምዕራፎች የሚጀምሩት፣ በ9፡3-27 በሚገኘውና ችግር ፈጣሪ በሆነው ከገባዖናውያን ጋር በተገባው ስምምነት ነው፡፡ ገባዖናውያን፣ በከነዓን እምብርት ውስጥ የሚኖሩ ሆነው ሳሉ፣ ከእስራኤል ጋር የሰላምን ቃል ኪዳን ለመጋባት ሲሉ፣ ከከነዓን ውጪ ከሩቅ

አገር እንደመጡ አስመስለው በመቅረብ እስራኤልን አሳቱ፡፡ ይህም ስምምት በተስፋፉቱ ምድር ደቡባዊ ክፍል ላይ እጅግ ከፍ ያለ ግጭት አስነሳ፡፡

በ10፡1-15 ላይ የተመዘገበው ይህ ሰፊ ግጭት፣ እስራኤል የመጀመሪውን ድል በደቡቡ ክፍል ላይ እንድትቀዳጅ አደረጋት፡፡ በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ እንደምናስተውለው፣ የኢያሩሳሌም ንጉሥ ከአምስት የደቡብ ነገሥታት ጋር ጥምረት በመፍጠር ገባዖናውያንን ወጋቸው፣ ገባዖናውያንም ወደ ኢያሱ ለእርዳታ ላኩ፡፡ ከስምምነታቸውም የተነሳ፣ እስራኤል ገባኦናውያንን መርዳት ግዴታ ሆኖባት ነበር፡፡ በዚህ የመጀመሪያ ደቡባዊ ጦርነት ላይም እግዚአብሔር ለኢያሱ ተዓምራዊ ድልን ሰጠው፡፡ ከዚያ ደግሞ፣ በኢያሱ 10፡16-43 ውስጥ፣ ኢያሱ በደቡባዊ ግዛቶች ላይ ያስመዘገባቸውን ድሎች፣ በደቡባዊ ጣምራ ጠላቶች ላይ በከታታይ ያስመዘገባቸውን የተለያዩ ድሎች ጸሐፊው በአጭር በአጭሩ ዘግቦልናል፡፡ በ10፡40 ላይ ጸሐፊአችን፣ "ኢያሱ ምድሪቱን ሁሉ … አጠፋ"

## በሰሜናዊ ጣምራ ጠላቶች ላይ የተገኙ ድሎች

በዚህ የመጽሐፉ ክፍል ውስጥ ቀጣዩ ዋና ክፍል በ11፡1-15 የሚገኘው ነው፡፡ በዚህ ስፍራ፣ ጸሐፊአችን ዘገባውን እስራኤል በሰሜናዊ ጣምራ ጠላቶች ላይ ወደተቀዳጀችው ድል ዘወር ያደርጋል፡፡ ይህም ክፍል ኢያሱ በደቡባዊው ክፍል ከተቀዳጀው ድል ጋር ተመሳሳይ የሆነ ዓይነት ንድፍ ያለው ሲሆን፣ ዘገባው ግን በጣም አጠር ያለ ነው፡፡ በቁጥር 1-11 ውስጥ፣ የአሦር ንጉሥ በእስራኤል ላይ ጣምራ ጠላቶችን እንዳስተባበረ እንመለከታለን፡፡ በ11፡4 ውስጥ፣ ጣምራ ጠላቶቹ "ከእጅግም ብዙ ፈረሰኞችና ሠረገሎች ጋር ወጡ፤ በባሕር ዳርም እንዳለ አሸዋ ብዙ ሕዝብ ነበረ።" ተብለው ተገልጠዋል፡፡ እግዚአብሔር ግን በእነዚህም በሰሜናዊ ጣምራ ጠላቶቻቸውም ላይ ድልን ለእስራኤል ሰጠ፡፡ ስለዚህ፣ በ11፡12-15 ውስጥ፣ ኢያሱ በሰሜናዊው ግዛቶች ላይ የተቀዳጃቸውን ወሳኝ ድሎች ማጠቃለያ እናገኛለን፡፡

እስራኤል በሁለቱ ጣምራ ጠላቶች ላይ የተቀዳጀቻቸውን ድሎች አወቃቀርና ይዘት በልቡናችን አድርገን፣ ወደ እነዚህ ምዕራፎች ቀደምት ትርጓሜ መለሰ በማለት ጥቂት ሃሳቦችን እንዳስሳለን፡፡

## ቀደምት ትርጓሜ

ቀደም ብለን እንዳየነው፣ እስራኤል ከኢያሪኮና ከጋይ ጋር ያደረገችው ውጊያ ለቀደምት ተደራሲያኑ ብዙ የሚያስተምረው ትምህርት እንዳለው ተረድተናል፡፡ ጸሐፊአችን ግን በኋለኞቹ ዘመናት የሚመጡት የእርሱ ተደራሲያን እነዚህን ምሳሌዎች እንደማይከተሏቸው በደንብ ያውቃል፡፡ ከተሞቹ ጥቂት ከተሞች፣ የጠላቶቻቸውም ቁጥር እስከዚህ ብዙ የማይባሉ ነበሩ፣ የእርሱ ተደራሲያን የሚገጥሟቸው ጣምራ ጠላቶች ግን በርካታ ሠራዊቶች የሚኖሯቸውና በጣም ጠንከር ያሉ ጣምራ ጠላቶች ናቸው፡፡ ስለዚህ ተደራሲያኑን በእንደዚያ ያለ ሁኔታ ውስጥ ሲያልፉ እንዲበረቱ ለማድረግ፣ ኢያሱ በእርሱ ዘመን ከተጋጠማቸው ከፍተኛ ጠላቶች ጋር ያደረገውን ውጊያና ድልም ሊያሳያቸው ይሞክራል፡፡

እስራኤል በሁለቱ ጣምራ ጠላቶቿ ላይ የተቀዳጀችው ድል ዘገባ ቀደም ባሉት ምዕራፎች ከተመለከትናቸው አምስት መሪ ሃሳቦች አራቱን ያሰምርባቸዋል፡፡

## መለኮታዊ ሥልጣን

በመጀመሪያ፣ እነዚህን ክንውኖች የከበባቸውን መለኮታዊ ሥልጣን እንመለከታለን፡፡ ለምሳሌ፣ በደቡብ በተመዘገበው የመጀመሪያ ድል፣ በ10፡8 ውስጥ፣ "እግዚአብሔርም ኢያሱን፦ በእጅህ አሳልፌ ሰጥቼአቸዋለሁና" ተብሎ ተጽፎአል፡፡ አንድ ሌላ ተጨማሪ ምሳሌ ብናነሳ፣ 11፡9 እንደሚነግረን፣ በሰሜን በቀዳጃቸው ድሎች፣ ኢያሱ እነዚያን እርምጃዎች ሁሉ የወሰደው፣ "እግዚአብሔር እንዳዘዘው ነው፡፡" እነዚህ ምዕራፎች ደግመው ደጋግመው አጽንኦት የሚሰጡት ኢያሱ በመለኮታዊ ሥልጣን የእስራኤል መሪ ስለመሆኑ ነው፡፡ እንግዲህ ይህ ዘገባ ቀደምት ተደራሲያኑ በራሳቸው ዘመን ጦርነት በሚገጥማቸው ወቅት ኢያሱ በእነዚህ ጣምራ ጠላቶቹ ላይ ከተቀዳጃቸው ታላላቅ ድሎች ትምህርትንና መመሪያን እንዲያገኙ ያስችላቸዋል፡፡

## የሙሴ ህግ ስነ-ልክ

ሁለተኛ፣ በሁለቱ ጣምራ ጠላቶች ላይ እስራኤል የተቀዳጀችው ድል በሙሴ ህግ ስነ ልክ ላይም አጽንዖት ይሰጣል፡፡ ለምሳሌ፣ ከገባዖናውያን ጋር የተደረገው ውል በተዘገበበት ታሪክ ውስጥ፣ በ9፡14 ላይ፣ እስራኤላውያን ተታልለው ነበር ምክንያቱም "ከእግዚአብሔር ምክርን አልጠየቁም ነበርና" ተብሎ ተጽፎ እናነብባለን፡፡ ዘዳግም 17፡9 በመሳሰሉ ምንባቦች ሙሴ የሰጠውን መመሪያ ባለማክበር ለእግዚአብሔር ታማኝ ያለመሆን ታይቶባቸዋል ያም የተገለጠው ከካህናት ምሪትን ባለመጠየቅ ነው፡፡ ግን፣ በኢያሱ 9፡20፣ "ስለ ማልንላቸው መሓላ" በማለት ኢያሱ የሙሴን ህግ ሲያከብር እናገኘዋለን፡፡

በተጨማሪም፣ እየተስፋፋ በመጣው የኢያሱ ደቡባዊ ክልል ድል ማጠቃለያ ውስጥ፣ በ10፡40 ላይ፣ "የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዳዘዘው" እስትንፋስ ያለውን ሁሉ በማጥፋት ኢያሱ የሙሴን ትዕዛዝ አክብሯል፡፡ በተመሳሳይ መንገድም፣ በሰሜናዊ ግዛት ድሉ ውስጥ፣ በ11፡12፣ ኢያሱ "የእግዚአብሔርም ባሪያ ሙሴ እንዳዘዘው … ፈጽሞም አጠፋቸው።" በ11፡15 ውስጥ፣ ኢያሱ፣ "እግዚአብሔርም ባሪያውን ሙሴን እንዳዘዘው እንዲሁ … ምንም አላስቀረም።" ኢያሱ በከነዓናውያን ላይ የተቀዳጃቸውን ድሎች ባጠቃለለበት ዳሰሳ ላይ፣ በ11፡20 ውስጥ፣ ኢያሱ "እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘ" አደረገ ይላል፡፡

እነዚህ መሪ ሃሳቦች የተሰመረባቸው ምክንያት በየዘመናቱ የሚመጡት እስራኤላውያን ድል የእነርሱ እንዲሆን የሚፈልጉ ከሆነ ለሙሴ ህግጋት ታማኝ ሆነው መዝለቅ እንደሚገባቸው ለማሳሰብ ነው፡፡ ልክ በኢያሱ ዘመን እንደነበረ ሁሉ፣ በእነርሱም ዘመን ህጉን መፈጸም በዘመናቸው ድልን ለመቀዳጀት እጅግ ቁልፍ ነገር ነው፡፡

## የእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል

ሦስተኛ፣ እስራኤል በሁለቱ ጣምራ ጠላቶች ላይ ያገኘችው ድል በእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል አማካይነት እንደሆነ እንደገና ተገንዝበናል፡፡ በመጀመሪያው ደቡባዊ ድል ውስጥ፣ 10፡10 እንደጠቆመን እግዚአብሔር ራሱ "በእስራኤል ፊት አስደነገጣቸው" ይላል፡፡ በቁጥር 11 ደግሞ፣ "እግዚአብሔር ከሰማይ ታላላቅ የበረዶ ድንጋይ አወረደባቸው" ይላል፡፡ ቁጥር 13 ደግሞ፣ "ፀሐይ ቆመ" ስለዚህም እስራኤል ጦርነቱን ድል አደረገች፡፡ እነዚህ መለኮታዊ ጣልቃ ገብነቶች ጸሐፊአችን በአድናቆት በቁጥር 14 ውስጥ "እግዚአብሔር ለእስራኤል ይዋጋ ነበር" እንዲል አድርጎታል፡፡ የእስራኤል ድል አድራጊነት ወደ ደቡባዊ ክፍል ሲስፋፋ ደግሞ፣ በ10፡21 ውስጥ፣ የእግዚአብሔር ኃይል ታላቅ ፍርሃት ሰዎች ላ እንዲወድቅ አድርጓል፣ ያም "በእስራኤል ልጆች ላይ ምላሱን ማንቀሳቀስ የደፈረ ማንም ሰው የለም።" ተብሎ ተገልጧል፡፡ ኢያሱም በ10፡25 ውስጥ፣ "እግዚአብሔር በምትወጉአቸው በጠላቶቻችሁ ሁሉ ላይ እንዲሁ ያደርጋልና" በማለት በድፍረት ተናግሯል፡፡ ጸሐፊው በ10፡42 ውስጥ ማጠቃለያውን፣ "የእስራኤልም አምላክ እግዚአብሔር ለእስራኤል ስለ ተዋጋላቸው" በማለት ይደመድመዋል፡፡

የእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ሃይል መሪ ሃሳብ በተጨማሪም በሰሜናዊ የእስራኤል ድል ወቅትም ተገልጦ እናገኛለን፡፡ ለአብነትም፣ በ11፡6 ውስጥ፣ "ሁሉን እንደ ሞቱ አድርጌ በእስራኤል እጅ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ"በማለት እግዚአብሔር ለኢያሱ አረጋግጦለታል፡፡ ከዚያም፣ በጣምራ ጠላቶቹ ላይ የተገኘው ድል ሲጠቃለልም፣ በ11፡20 ውስጥ፣ "ልባቸውን እንዲያደነድኑ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነ።" ይላል፡፡ ይህም በመሆኑ የእስራኤል ጠላቶች ተሸናፊ ሆኑ ማለት ነው፡፡

ጸሐፊው ይህንን መሪ ሃሳብ ደጋግሞ የማንሳቱ ጉዳይ ዓላማ ያደረገው ቀደምት ተደራሲኑ ግጭት በሚገጥማቸው ወቅት በራሳቸው ኃይል በፍጹም እንዳይታመኑ አስረግጦ ለማስረዳት ነው፡፡ በጠላቶቻቸው ላይ ድልን የመቀዳጀታቸው ብቸኛ ተስፋ እግዚአብሔር የእነርሱ ምትክ ሆኖ በመለኮታዊ ኃይሉ በውጊቸው ውስጥ ጣልቃ የሚገባላቸው መሆኑ ነው፡፡

*እግዚአብሔር በልእለ-ተፈጥሮአዊ ኃይሉና ሥልጣኑ ለኢያሱና ለእስራኤላውያን ድልን ሰጣቸው፡፡ እግዚአብሔር "ምድሪቱን ሰጣቸው" ወይም "ምድሪቱን በእጃቸው አሳልፎ ሠጣቸው" የሚለው መግለጫ፣ በዕብራይስጡ ተመሳሳይ ግሥ ነው፣ በኢያሱ መጽሐፍ ደግሞ በርካታ ጊዜ ተደጋግሞ ተጠቅሷል፡፡ ጠላቶቹን በኢያሱ እጅ አሳልፎ የሰጠው እግዚአብሔር ራሱ ነው፡፡ ምድሪቱንም ለእስራኤል አሳልፎ የሰጠው ራሱ ነበር፡፡ ይህ ሃሳብ የተደጋገመው እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ፣ ጠላቶቹንም ድል የሚያደርግ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ የአሞራውያን ነገሥታት በገባዖን ሰዎች ላይ በተነሱባቸው ወቅት፣ የገባዖን ሰዎች እነዚህን ነገሥታት ለመግጠም ኢያሱን ጠይቀው ነበር፡፡ ውጤቱንም በኢያሱ 10፡11 ላይ እናነብበዋለን፡፡*

*ከእስራኤልም ልጆች ፊት እየሸሹ በቤትሖሮን ቍልቍለት ሲወርዱ፥ ወደ ዓዜቃ እስኪደርሱ ድረስ እግዚአብሔር ከሰማይ ታላላቅ የበረዶ ድንጋይ አወረደባቸውና ሞቱ፤ የእስራኤል ልጆች በሰይፍ ከገደሉአቸው ይልቅ በበረዶ ድንጋይ የሞቱት በለጡ። (ኢያሱ 10፡11)*

*በዚህ ስፍራ አጽንኦት የተሰጠው ነገር የእግዚአብሔር ሥልጣን ነው፡፡ በዚህ ሁነት ውስጥ እግዚአብሔር ሥልጣኑን ገልጧል፡፡ በጠላቶቻቸው ላይ፣ ደንጋዮችን ወረወረባቸው፣ የበረዶ ድንጋዮችንም አዘነበባቸው፣ በእስራኤላውያን ሰይፍ ከሞቱት ይልቅ በእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት የሞቱት ቁጥር እጅግ በለጠ፡፡ እናም፣ በዚህ ስፍራ የተገኘው ድል፣ ያለምንም ጥርጥር በሁኔታዎቹ ላይ በቀጥታ ጣልቃ በገባው በእግዚአብሔር የተገኘ ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ድል ነው፡፡ ይህም ሁኔታ በሁሉም ነገር ላይ እና በሁሉም ሁኔታ ውስጥ የማይገደብ ኃይልና ሥልጣን ስላለው ስለ ሁሉ ቻዩ አምላካችን ስለ እግዚአብሔር አስደናቂ ትምህርት ይሰጠናል፡፡*

*ሬቨረንድ፣ ሸሪፍ ጌንዲ፣ በትርጉም የቀረበ*

## እስራኤል በጠቅላላ

እስራኤል በሁለቱ ጣምራ ጠላቶቿ ላይ ያገኘቻቸውን ድሎች ጸሐፊአችን ሲዘግብ አራተኛውንም መሪ ሃሳብ አጽንዖት ይሰጥበታል፡፡ በገባኦን አቅራቢያ በተገኘው የመጀመሪያ ድል፣ በ10፡7 ውስጥ፣ "ኢያሱም ከእርሱም ጋር የነበሩ ሰልፈኞች ሁሉ ጽኑዓን ኃያላኑም ሁሉ ከጌልገላ ወጡ።" ይላል፡፡ በ10፡15 ውስጥ ደግሞ፣ "እስራኤል ሁሉ" ከኢያሱ ጋር ከውጊያ ተመለሱ ይላል፡፡ በደቡባዊ ግዛት ድላቸውን እያሰፉ ሲመጡ፣ በ10፡21 ውስጥ፣ "ህዝቡ ሁሉ" ከኢያሱ ጋር ነበሩ ይላል፡፡ በ10፡24 ውስጥ ደግሞ፣ ኢያሱ "የእስራኤልን ሰዎች ሁሉ" ጠራ ይለናል፡፡ የዚህን መሪ ሃሳብ ወሳኝነት በ10፡29-38 ላይም እንመለከተዋለን፡፡ በዚያ ስፍራ፣ ጸሐፊአችን፣ "ከዚያም ኢያሱና እስራኤል ሁሉ …" ያንንና ይህንን አደረጉ በማለት ደጋግሞ ይጠቅሰዋል፡፡ በ10፡43 ውስጥ ደግሞ፣ "እስራኤል ሁሉ" ከኢያሱ ጋር ተመለሱ በማለት ይህ ክፍል ይደመደማል፡፡ በመጨረሻም፣ በእስራኤል ሰሜናዊ ድል፣ በ11፡7 ውስጥ፣ "ኢያሱም ከሰልፈኞቹ ሁሉ ጋር" አብረው እንደነበሩ ያመለክተናል፡፡

እስራኤላውያን ደግመው ደጋግመው እንደ አንድ ህዝብ መቆም እንደሚያዳግታቸው የኢያሱ መጽሐፍ ጸሐፊ ያውቃል፡፡ ስለዚህ፣ በኢያሱ ዘመን አንድ ሆነው በመቆማቸው ያገኙዋቸውን በረከቶች አጽንኦት ሰጥቶ ይዘግባል፡፡ ቀደምት ተደራሲያኑም በራሳቸው ዘመን ከጠላቶቻቸው ጋር ሲገጥሙ በአንድነት እንዲቆሙ ጥሪውን ያቀርብላቸዋል፡፡

እስራኤላውያን ድል አድርገው የመውረሳቸው ጉዳይ ለድል ያደረጉትን ዝግጅት፣ በሁለቱ ከተሞች ላይ የተገኙ ድሎችና በሁለቱ ጣምራ ጠላቶች ላይ የተገኙትን ድሎች እንዴት እንደሚካትት ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ በዚህ ትምህርታችን፣ ስለ እስራኤል ድል የተጻፈው ዘገባ የሚኖረውን ክርስቲያናዊ ተዛምዶ ወደመመልከቱ እንሸጋገር፡፡

# ክርስቲያናዊ ተዛምዶ

በታሪክ ዘመናት መካከል፣ እውነተኛ የክርስቶስ ተከታዮች ደግመው ደጋግመው ይህንን የኢያሱን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ ጽንፎች ይመለከቱታል፡፡ አንዳንዶቹ፣ ይህ ክፍል ዛሬ ከእኛ ጋር ምንም የሚያገናኘው ነገር የሌለ የብሉይ ኪዳን ክፍል ብቻ ነው በማለት ያጣጥሉታል፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ የክርስቶስ ለሆነው ጉዳይ እጆችን በአንድነት የማስተባበር አስፈላጊነት ሃሳባቸውን ለማጽናት ይጠቀሙበታል፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ የእስራኤላውያን በድል የመውረስ ሙላት የመሆኑን አዲስ ኪዳናዊ አስተምህሮ ስንመለከት፣ ይህ የኢያሱ መጽሐፍ ክፍል በትክክኛው መንገድ እንዴት ክርስቲያናዊ ተዛምዶውን እንደሚያገኝ እንመለከታለን፡፡

ይህ ክፍል የሚኖረውን ክርስቲያናዊ ተዛምዶ የምንቃኘው ባለፉት ትምህርቶች ባየናቸው ሃሳቦቸ ላይ በመገንባት ሲሆን፣ ሃሳቡም፡ ክርስቶስ የመንግሥቱን መምጣት ሲያበስር የእስራኤልን በድል የመውረሰ ታሪክ ፈጽሞታል የሚል ነው፡፡ በመንግሥቱ መስፋፋትም ውስጥ ፈጽሞታል፡፡ አንድ ቀን ደግሞ የክርስቶስን መንግሥት ወደ ፍጻሜው ሲያመጣ ሁሉን ወደ ሙላት ያደርሳል፡፡

# የመንግሥቱ ብሥራት

በጥቅሉ፣ በኢያሱ ዘመን የተከናወነው የእስራል ድል አድራጊነት፣ የሚወክለው በእግዚአብሔርና በሰይጣን ደግሞም በእርሱ ተከታዮች መካከል የሚካሄደውን ፍልሚያ ነው፡፡ በኢየሱስ የመጀመሪያ መምጣት ወቅት፣ እርሱ እና የመጀመሪው ክፍለ ዘመን የእርሱ ሐዋርያት ከመንግስቱ ብሥራት እጅግ የበለጠ ተግባር አከናውነዋል፡፡ ወንጌላትና የሐዋርያት ሥራ መጻሕፈት እንደሚያሳዩን ኢየሱስና ሐዋርያቱ ከሰይጣንና ከክፉ መናፍስት ጋር በቀጥታ እንደተፋለሙ ያስተምሩናል፡፡ ደቀመዛሙርቱ አጋንንትን ካስወጡ በኋላ ወደ ኢየሱስ ተመልሰው ሳለ፣ በሉቃስ 10፡18፣ ላይ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፣ “ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ።” ከዚህም በበለጠ፣ ቆላስይስ 2፡15፣ ዕብራውያን 2፡14፣ 15፤ እና ኤፌሶን 4፡8 የመሳሰሉ ምንባቦች እንደሚያስተምሩን፣ የኢየሱስ ሞት፣ ትንሣኤና እርገት ሰይጣንንና መናፍስቱን ድል አድርጓቸዋል፡፡ ኢየሱስ ከኢያሱ እጅግ በሚልቅ መንገድ የእርሱ ሐዋርያት በአህዛብ መንግሥታት ምድሮችም ውስጥ እንኳን ሳይቀር አጋንንትን እያሳደዱ የሚያስወጡበትን መንገድ ይከፍትላቸው ነበር፡፡

ግን፣ ኢየሱስ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ፣ ኢያሱ እንዳደረገው በኃጢአተኞች ላይ ጦር አላስከተተም፣ ምክንያቱም ያ ጊዜ ኢየሱስ በኃጢአተኞች ላይ ጦር ሚያነሳበት የእግዚአብሔር ጊዜ አልነበረምና ነው፡፡ እንዲያውም፣ ጴጥሮስ አካላዊ ሰይፍ በመምዘዙ ኢየሱስ እንደገሰፀው ዮሐንስ 18፡11 ይነግረናል፡፡ ይልቁኑ ኢየሱስ፣ በሰይጣን እና በተከታዮቹ ላይ የእግዚአብሔርን ድል ያወጀው በባለ ሁለት ወገን የምንግሥቱ ወንጌል ወይም “የምሥራች” አማካይነት ነው፡፡ እጅግ በብርቱ ስለሚመጣው የእግዚአብሔር **ፍርድ** አስጠንቅቋል፣ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ለማንበርከክ ፈቃደኛ ለሆኑት ደግሞ **ምህረት**ን ሰጥቷል፡፡ በመጀመሪያው ዘመን የነበሩ ሐዋርያትና ነቢያትም ይህንን የመጀመሪያ የክርስቶስን ዓለም አቀፋዊ ድል አድራጊነት በሚያስፋፉበት ወቅት ያደረጉት ከዚህ ጋር እጅግ ተመሳሳይ የሆነውን ነገር ነበር፡፡ መቼም ቢሆን በሰዎች ላይ አካላዊ ጦርነትን አውጀው አያውቁም፡፡ ይልቁኑ፣ ልክ እንደ ኢየሱስ፣ የፍርድንና የድነትን የወንጌል መልእክት አስፋፍተዋል፡፡

እንግዲህ፣ አዲስ ኪዳን ስለሚመጣው የእግዚአብሔር ፍርድ ከቤተክርስቲያን ውጪ የሚገኙትን የማያምኑ ሰዎች ደግሞ ደጋግሞ ያስጠነቅቃል፡፡ በተጨማሪም ደግሞ “*ሐሰተኛ ወንድሞችን*” ወይም “*በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ*”

ግን የማያምኑ ሰዎችንም ስለ እግዚአብሔር ፍርድ አስጠንቅቀዋል፡፡ 1ኛ ቆሮንቶስ 16፡22 እና ገላትያ 1፡8 የመሳሰሉ ምንባቦች በቤተክርስቲያን ውስጥ በሚገኙ የሐሰት መምህራን ላይ ስለሚመጣው እርግማን በግሪኩ አናቴማ *anathema* (ἀνάθεμα) ያስጠነቅቃሉ፡፡ እነዚህም እርግማኖች በእስራኤላዊው አካን ላይ የወረደውን ፍርድ ማለትም “ሙሉ በሙሉ እንዲወድም” የተደረገበትን ሁኔታ ያስታውሱናል፡፡ ይህም ተዛምዶ በሰፕቱዋጀንቱ የኢያሱ ቅጂ- በጥንታዊው የግሪክኛ ቅጂ ማለት ነው - አናቴማ የተሰኘው ቃል የሚፈታው ቻርም *charam* (חָרַם) እና ቼሬም *cherem* (חֵרֶם) የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን ትርጓሜውም “ሙሉ በሙሉ መውደም” ማለት ነው፡፡ ሆኖም ሐዋርያትና ነቢያቱ በቤተክርስቲያንና ከቤተክርስቲያን ውጪ ስለ እግዚአብሔር ፍርድ ማስጠንቀቂያ የመስጠታቸውንም ያህል፣ እያንዳንዱ ሰው ከሚመጣው የእግዚአብሔር ፍርድ ያመልጥ ዘንድ ንስሓ እንዲገባም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

> *በኢያሱ መጽሐፍ ውስጥ ሰዎች ተረግመዋል፡፡ ከህዝብ መካከል ተለይተው እንዲወጡ ተደርገዋል፣ ደግሞም ፈጽመው እንዲጠፉም ተደርገዋል፡፡ ያም የመጣባቸው እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ ስላላከበሩ ስላላከበሩ፣ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ስላልጠበቁ እና እግዚአብሔር እንዲመላለሱባቸው በሚፈልገው መጠን ስላልተመላለሱ ነበር፡፡ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች አመለካከት ጉዳዩ መልካም፣ ፍትሃዊና ጽድቅ ያለበት ነው፡፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ጻድቅ ባህርይ ከፍ ስለሚያደርግ፣ እግዚአብሔር ለህዝቡ የሰጠውን ተስፋ ስለሚያጎላ፣ ደግሞም እግዚአብሔር ራሱ በእውነት የሚታመን መሆኑን ያሳያል፡፡ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 16፡22 እና በገላትያ 1፡8 ውስጥ እንዲህ ይላል፣ እግዚአብሔርን ካልወደዳችሁ፣ ወንጌልን አትሰብኩም፣ እንግዲያው የእግዚአብሔር ፍርድ በእናንተ ላይ ነው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ጳውሎስ እያደረገ ያለው ምንድን ነው? ብንል፣ “እርሱ የተረገመ ይሁን?” በማለት ከእግዚአብሔር ፍትህ ጋር እየተስማማ ነው፡፡ ያም የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን የፍጻሜ መምጣት፣ በመምጣቱም ጠላቶቹን ሁሉ በፍርዱ ስር ያደርጋል፣ የእግዚአብሔርንም ጽድቅ ይገልጣል ደግሞም የእግዚአብሔርን ተስፋዎች እውነትነት ያጸናል፡፡ ጌታን የሚወድዱ ሰዎች ደግሞ፣ የእግዚአብሔር ፍትህ ሲሰፍን፣ እና ሲከበር፣ ደግሞም እግዚአብሔር የቃሉን እውነተኝነት እንዲገልጥ ይፈልጋሉ፡፡*
>
> *ዶ/ር ጀምስ ኤም፣ ሃሚልተን*

እነዚህን መሰረታዊ ሃሳቦ በልቡናችን ስናደርግ፣ የኢያሱ መጽሐፍ የዚህ ክፍል አምስቱ ዋና መሪ ሃሳቦች በክርስቶስ መንግሥት ብስራት ውስጥ እንዴት ወደ ሙላት እንደመጡ የምናስተውልበትን በርካታ እድሎች እናገኛለን፡፡ የኢያሱ ድል በመለኮታዊ ሥልጣን እንደተመራ ሁሉ፣ የኢየሱስና የሐዋርያቱም ድሎች የተመሩት በዚያው መለኮታዊ ሥልጣን ነው፡፡ በኢያሱ ዘመን የተገኘው ድል በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ላይ እንደተመሠረተ ሁሉ፣ የኢየሱስና የሐዋርያቱም ድሎች መሠረታቸውን ያጸኑት በአዲሱ ቃል ኪዳን ላይ ነው፡፡ ለኢያሱ ድል ማድረግ የሙሴን ህግ ልኬቶች መታዘዝ ቅልፍ ነገር እንደነበረ ሁሉ የኢየሱስና የሐዋርያቱም ስኬት ለሙሴ ህግጋትና ከሙሴ በኋላ ለመጣው ሙሉ መገለጥ ራስን መስጠትና መታዘዝ እጅግ ቁልፍ ነገር ነው፡፡ ኢያሱና እስራኤል በእግዚአብሔር ልእለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል ላይ እንደታመኑ ሁሉ፣ የኢየሱስና የሐዋርያቱም ድሎች በእግዚአብሔር ልእለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል ላይ የሚደገፍ ይሆናል፡፡ የኢያሱ ድል እስራኤልን በጠቅላላ እንዳካተተ ሁሉ፣ ኢየሱስም በመላው እስራኤል የሚገኙ ሰዎችን ሁሉ አብረውት እንዲሆኑ ይጠራ ነበር፡፡ በበዓለ ሃምሳ ቀን፣ እርሱ ከክፉ ጋር ባደረገው ውጊያ ከእርሱ ጋር የሚተባበሩ ከመላው ዓለም የተሰባሰቡ ሰዎች ነበሩ፡፡ የኢየሱስ ሐዋርያትና ነቢያትም በመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን ዘመን ቁጥራቸወ በርካታ የሆኑ አህዛብን አብረዋቸው አሰልፈው ነበር፡፡

የእስራኤል በድል አድራጊነት የመውረስ ታሪክ ክርስቲያናዊ ተዛምዶ በክርስቶስ መንግሥት ብስራት ወቅት እንዴት ወደሙላት እንደመጣ ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ በመንግሥቱ መስፋፋት ወቅት በክርስቶስ እንዴት ሙላቱን እንዳገኘ ወደመመልከቱ እንሸጋገራለን፡፡

# መስፋፋት

እንደ 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡25 አገላለጽ ኢየሱስ "ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች እስኪያደርግ ድረስ" ሊነግሥ ይገባዋል፡፡ በዚሕም ምክንያት ላለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት በቤተክርስቲያኑ አማካይነት በሚሰጠው አገልግሎት ዓለም አቀፋዊ ድሉን በምድር ላይ በሚገኙ መንግሥታት ሁሉ ውስጥ በተሳካ ሁኔታ እያስፋፋ ነው፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ደግሞ፣ ቤተክርቲያን ንስሓ መግባትንና፣ ጸጋን ለመቀበል የምትችልበትን የቃል ኪዳን ተሃድሶ ማድረግ ሲሳናት ከቁጥር በላይ የሆኑ እንቅፋቶችንም አሳልፋለች፡፡ ስለዚህ፣ በየዕለቱ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ክርስቶስ የጀመረውን መንግሥቱን እንድናስፋፋ አዲሰ ኪዳን ጥሪ ያቀርብልናል፡፡

በአንድ በኩል፣ ኢየሱስ፣ ሐዋርያቱና ነቢያቱ እንዳደረጉት ሁሉ፣ እኛም ሰይጣንና ክፉ መናፍስቱን ለመዋጋት በሚያስችለን መንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ መሳተፋችንን በሙላት ልንቀጥል ይገባናል፡፡ እንደ ኤፌሶን 6፡13-18 አገላለጽ፣ "የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልናነሣ... የእውነትን ቀበቶ ልንታጠቅ... የጽድቅ ጥሩር ልንለብስ ... የሰላምን ወንጌል ልንጫማ ... የእምነትን ጋሻ ንናነሳ ... የመዳንን ራስ ቁር ልናጠልቅ ... የመንፈስን ሰይፍ ልንይዝ እና በመንፈስ አዘውትረን ልንጸልይ" ይገባናል፡፡ ልክ እስራኤል የከነዓንን ምድር ድል ለማድረግ ተገቢ ዝግጅት አድርጋ እንደነበረች ሁሉ እኛም ለመንፈሳዊ ውጊያ ትክክልኛ ዝግጅት ማድረግ ይገባናል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ልክ ኢየሱስና ሐዋርያቱ እንዳደረጉት እኛም ሰዎችን ሁሉ በዚሁ ስራ ተሳታፊ ማድረጋችንን ልንቀጥል ይገባናል፡፡ የክርስቶስን መንገድ የሚቃወሙትን ሁሉ እንዋጋቸዋለን፣ ሆኖም በአካላዊ ጥቃት አይደለም፡፡ ይልቁኑ፣ የክርስትናን የፍርድና የምህረት ወንጌል ልንሰብክ ይገባናል፡፡ በማያምነው ዓለም ላይ ስለሚመጣው የእግዚአብሔር ፍርድ ማስጠንቀቂያ ልንሰጥ ይገባናል፡፡ ኢያሱ እስራኤላዊው አካን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ሲዋጋ አስቀድሞ እንዳስጠነቀቀው ሁሉ እኛም በቤተክርስያን ውስጥ የሚገኙትን የሐሰት መምህራን ስለ መጪው የእግዚአብሔር ፍርድ ልናስጠነቅቅ ይገባናል፡፡ በ2ኛ ቆሮንቶስ 10፡5 ውስጥ፣ ጳውሎስ አገልግሎቱን "በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ" የሚያፈርስ አድርጎ እንደገለጸው ሁሉ ማለት ነው፡፡ ንስሓ ለሚገቡና ራሳቸውን ለክርስቶስ ለሚሰጡ ሁሉ የመዳንን ተስፋ ልናውጅ ይገባናል፡፡

የክርስቶስ መንግሥት የመስፋፋቱ እውነታ እኛም የኢያሱን ድል ታሪክ በዕለት ከዕለት ሕይወታችን የምናዛምድበትን መንገድ እንድናስተውል ያደርገናል፡፡ ልክ እስራኤል በእግዚአብሔር መለኮታዊ ሥልጣን እንደተመራች ሁሉ፣ እኛም የክርስቶስን መንግሥት በምናስፋፋበት ወቅት በመለኮታዊ ሥልጣን ልንመራ ይገባናል፡፡ እስራኤል ድሏ አስተማማኝ የሚሆነው በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ላይ ሲመሰረት እንደነበረ ሁሉ፣ እኛም በአዲሱ የክርስቶስ ኪዳን ምክንያት የበለጠ መተማመን ሊኖረን ይገባል፡፡ እስራኤል በጦርነት ድል የማድረጓ ነገር የሚመሠረተው ለሙሴ ህግጋት ራሳቸውን በሰጡበት ልክ እንደሆነ ሁሉ፣ በክርስቲያናዊ ውጊያዎቻችን ለቅዱሳት መጻሕፍት ልኬት ሁሉ ማለትም ለብሉይም ለአዲስም በሚኖረን መሰጠት ልክ ይሆናል፡፡ የእስራኤል ድል የተገኘው በእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃል እንደነበረ ሁሉ፣ ዛሬም የእኛ ድል የሚገኘው በእግዚአብሔር መንፈስ ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል አማካይነት ነው፡፡ በኢያሱ ዘመን በተገኘው ድል እስራኤል በጠቅላላ እንደተሳተፈች ሁሉ ዛሬም እኛ ውጊያችንን ልንዋጋ የምንችለው ከቋንቋና ከህዝብ እንደ አንድ ሰው ሆነን በመሰለፍ ነው፡፡

የእስራኤል ድል ክርስቲያናዊ ተዛምዶ የሚወራረሰው ክርስቶስ በመንግሥቱ ብሥራት ወቅት ካደረገው ነገር ጋር እና በመንግሥቱ መስፋፋት ወቅት አሁን እያደረገ ካለው ነገር ጋር ብቻ አይደለም፡፡ በተጨማሪም የኢያሱ ዘገባ ክርስቶስ ዳግመኛ ተመልሶ በሚመጣበት ወቅት በመንግሥቱ ፍጻሜ ወቅት ከምንጠብቀው ተስፋም ጋር እናዛምደዋለን፡፡

# ፍጻሜ

አዲስ ኪዳን፣ ኢየሱስ ተመልሶ በሚመጣበት ወቅት እንደ ድል አድራጊ ንጉሥ እንደሚመጣ የሚነግረን ያለምንም ማጠራጠር ነው። በራዕይ 19፡11 ዮሐንስ ባየው ራእይ ውስጥ፣ ኢየሱስን ያየው እንደ “ፋጅና ተዋጊ” ሆኖ ነው። በዚያችም ቀን፣ የኢየሱስ ድል ክርስቶስ በመላው ዓለም ላይ የሚቀዳጀውን የድል ተስፋ ፍሬ አፍርቶ እንድናይ ያደርገናል። በኢያሱ ዘመን ከተደረገው ትልቅ ጥፋት ይልቅ በኢየሱስ የሚከናወነው እጅግ ይልቃል። ኢያሱ በእርሱ ዘመን ለህዝቡ ካመጣው በጎ ትርፍ ይልቅ ኢየሱስ የሚያመጣው እጅግ ይልቃል።

በአንደ በኩል፣ ክርስቶስ ሲመለስ፣ ሰይጣን ለአንዴና ለመጨረሻ ይሸነፋል። ከዚያ በኋላ እኛን የሚያታልልበትም ሆነ የሚጎዳበት ኃይል አይኖረውም። ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 16፡20 እንደጻፈው፣ “የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል።” በሌላ በኩል ደግሞ፣ አመጻኛ በሆኑ የሰዎች ልጆች ላይ እግዚአብሔር ሚኖረው ምህረትም ያበቃል። ኢየሱስ ራሱ በራእይ 21፡8 እንደተናገረው፣ “ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤” ደግሞም ሰይጣንን ሲያገለግሉ የነበሩ ሁሉ ከምድር ይወገዳሉ፣ ራሳቸውን ለክርስቶስ ያስገዙ ሁሉ ደግሞ በአዲስ ሰማይና ምድር የዘላለም መዳንን የከበረ ድል ያጣጥማሉ።

> *እኛ ዛሬ የምንኖረው ትልቅ ፍልሚያ እና ውጥረት፣ መከራ፣ ስደት፣ ውስጥ ነው። ስለዚህ ይህ ሁኔታ እንዴት ሊለወጥ ይችላል? ብሎ መጠየቅ ተፈጥሮአዊ ጥያቄ ነው። የኢየሱስ ዳግመኛ መመለስ ከመጀመሪያው መምጣቱ ጋር የተለየ እንደሆነ ማረጋገጥ እንፈልጋለን። በዚያም ቀን ስለ ፍትህ ያለን ጩኸት እንደሚያከትምና ሁሉ ነገር እንደሚያበቃ እርሱም ሁሉን ትክክል ያደርጋል። በከፊሉም፣ ያንን ነገር እናምናለን፣ ግን ገና በሙላት አላየነውም። የምንታመነው እግዚአብሔር እግዚአብሔር ስለሆነ፣ በመጨረሻውም ዘመን እርሱ ያው ሆኖ ስለሚዘልቅ ነው። እውነቱን ስንናገር፣ ፍጥረት ሁሉ በፍጥረትነቱ የነበረበት የተበላሸ ማንነቱ ያከትማል፣ እግዚአብሔርም ፍጹም ፍትሁን ያሰፍናል፤ እንከን የለሽ ፍርዱንም እግዚአብሔር ይገልጻል። ፍርዱ ግን ጭካኔ የምላበት አይደለም። የሚፈርደውም በፍትህ ስነ-ልክ መሠረት ነው።* ስለዚህም፣ ሞት የተባለው ሁሉ ድል ይነሳል። ጣዖቶቻችን በጠቅላላ ያከትምላቸዋል። ሁሉ ትክክል ይሆናል። በሰው ዘር በጠቅላላ ይህን እውን ሆኖ ከማየት የሚበልጥ ናፍቆት የለውም፣ እርሱንም በናፍቆት በመጠበቃችን ምንም ስህተት የለበትም ምክንያቱም ሁሉ እግዚአብሔር እንደተናገረው እንደዚያው ይፈጸማልና ነው።
>
> *ዶ/ር ሪቻርድ ሊንትስ*

ልክ መለኮታዊው ሥልጣን የኢያሱን ተግባራት ይመራ እንደነበረ ሁሉ፣ ታላቅና አስፈሪ ሆነውንም የኢየሱስን መመለስ የሚመራውም የእግዚአብሔር ሥልጣን ነው። የኢያሱ ድል እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ከገባው ቃል ኪዳን ጋር የተሳሰረ እንደሆነ ሁሉ፣ እግዚአብሔር በአዲሱ ኪዳን የገባው ቃል ጽኑ በመሆኑ የክርስቶስ የፍጻሜ ድል የተረጋገጠ ነው። የእስራኤል ስኬት የተመሰረተው በሙሴ ህግጋት ስነ-ልክ ላይ እንደሆነ ሁሉ፣ የኢየሱስ የፍጻሜ ድልም ይሳካል ምክንያቱም እርሱ አንዳች እንከን የለበትምና ነው። የኢያሱ ድል ከእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል እንደተገኘ ሁሉ፣ የኢየሱስ መመለስም የእግዚአብሔርን ታላቅ ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል ዓለም ከዚህ ቀደም ዐይታው በማታውቀው መጠን የሚገልጥ ይሆናል። የኢያሱ ድል የእስራኤልን ሁሉ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንደጠየቀ ሁሉ፣ ክርስቶስ ሲመለስም፣ በምድር ሁሉ ላይ የሚኖሩ የእግዚአብሔር ሰዎች ከየነገዱ ሁሉ ተሰብስበው እንደ አንድ ሰው የእርሱን ታላቅ ድል ያከብራሉ።

# ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት፣ የኢያሱ መጽሐፍ የመጀመሪው ዋና ክፍል በእስራኤል ድል አድርጎ መውረስ ሃሳብ ላይ እንደሚያተኩር መርምረናል፡፡ የኢያሱ መጽሐፍ ጸሐፊ እስራኤል ለድል ያደረገችውን ዝግጅት እንዴት እንደዘገበው፣ እስራኤል በሁለቱ ከተሞች ማለትም በኢሪኮና በጋይ ላይ ያገኘችውን ድል እንዴት በንጽጽር እንዳቀረበው፣ ደግሞም በተስፋዪቱ ምድር ደቡባዊና ሰሜናዊ ግዛት ውስጥ በሚገኙ ኃያላን ጠላቶች ላይ እስራኤል የተቀዳጀችውን የማያዳግም ድል እንዴት እንዳሰፈረው መርምረናል፡፡ ደግሞም የመጽሐፋችን ይህ የመጀመሪያ ክፍል ያነሳቸው ሃሳቦች ክርስቲያናዊ ተዛምዶ ሊደረግባቸው የሚችልባቸውን መንገዶች በጥቂቱ ዳስሰናል፡፡

መጽሐፈ ኢያሱ ቀደምት ተደራሲኑ በሚኖሩበት ዘመን በሚገጥሟቸው ውጊዎች ሊተገብሯቸው ሚችሉ ወሳኝ አመለካከቶችን  አስፍሯል፡፡ ይህንንም ያደረገው እስራኤል የተስፋዪቱን ምድር ለመውረስ ባደረገችው ፍልሚያ ምን እንደተካሄደ በማሳሰብ ነው፡፡ ይህ ዘገባ እስራኤል በኢያሱ ዘመን ያሳካችውን በመመልከት እኛም በክርስቶስ የፍጻሜ ድል ውስጥ በምንሳተፍበት ወቅት ተገቢውን መመሪያ እንድናገኝ ያስችለናል፡፡ ክርስቶስ ባረጋገጠው ድል ላይ እንድንተማመን ጥሪን ያቀርብልናል፡፡ በዕለት ከዕለት በሚገጥመን ውጊያ ውስጥ እርሱን እንድንከተል ጥሪ ያቀርብልናል፡፡ ዛሬ የሚገጥመን ፈተና  ምንም ይሁን ምን፣ ክርስቶስ ዳግመኛ ይመጣል ከፉውንም ድል አድርጎ ፍጥረትን ሁሉ ያሳርፋል፡፡